# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 136 ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## «በሀገራዊ ምክክሩ ከ40 በላይ ፓርቲዎች አብረውን ለመስራት ተስማምተዋል»

- ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

በዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ከ40 በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር ለመስራት መስማማታቸውን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ገለፁ።

ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሚዘጋጀው ዘመን መጽሔት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ ተፎካካሪዎቹን እና ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡት 53 የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ከ40 በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር ለመስራት ተስማምተዋል።

ከ40 በላይ ከሆኑት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አብረን ለመስራት ስምምነት ላይ እስከንደርስ ድረስ የራሳቸው ጥርጣሬ ነበራቸው ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ አንዳንዶቹ በአዋጁ አቀራረጽ ሂደት ላይ እንዲሁም በኮሚሽኑ ስም ላይ

«በሀገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






## በደንበል ሐይቅ ዳርቻ የሚገነባው የ100 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል

ሳሙኤል ወንደሰን



ባቱ፡- የባቱ ከተማን የቱሪስት ቁጥር የሚጨምር የአንድ መቶ ሚሊየን ብር ፕሮጀክት በዘንድሮ ዓመት እንደሚጠናቀቅ የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ ደጀኔ አስታወቁ።

የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ ደጀኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በደንበል ሀይቅ ዳርቻ የሚገነባው የአንድ መቶ ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት የባቱ ከተማን የቱሪስት ፍሰት ቁጥሩን የሚጨምር ነው። ፕሮጀክቱን በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው።

በደንበል ሐይቅ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## በዞኑ 97 በመቶ ሰብል ተሰብስቧል

- 368 ሺህ ሄክታር መሬት በክላስተር ለምቷል
- 22 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

በፀጋዬ ጥላሁን

ደብረማርቆስ፡- በምስራቅ ጎጃም ዞን በ2014/2015 የመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ከ616 ሺህ 489 ሄክታር መሬት 97 በመቶ ሰብል ተሰብስቧል።

የምስራቅ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ

በዞኑ 97 በመቶ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ሲቪል ማህበራት በመልሶ ግንባታ ሥራዎች በጋራ እንዲሳተፉ ጥሪ ቀረበ



ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

በጌትነት ተስፋማርያም

መቀሌ፡- ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ሲቪል ማህበራት በመልሶ ግንባታና ማቋቋም ሥራዎች ላይ በጋራ እንዲሳተፉ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ጥሪ አቀረበ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በትግራይ ያለው የሰብዓዊ፣ መልሶ ግንባታና መልሶ ማቋቋም ጉዳዮችን በተመለከተ ትላናንት በትግራይ ክልል ካሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ውይይት አድርጓል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ዶክተር ንጉሱ ለገሠ እንደገለጹት፤ በትግራይ ከሚገኙ የሲቪክ ማህበራት ጋር በጋራ በመተባበር የሰብዓዊ ድጋፍና መልሶ ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ።

በዚህ የልማትና ድጋፍ ሥራ ላይ አቅሙ ያላቸው

ከሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








በመዲናዋ ተገጣጣሚ ቤቶችን ለመገንባት 30 ህንፃ ተቋራጮች እየተሳተፉ ነው

ገጽ 3

# የመታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት ተቸግረናል

*- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች*

# የአገልግሎት መቆራረጥ ችግሩን የሚቀርፍ ሲስተም እየለማ ነው

*- የከተማ አስተዳደሩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ*

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በወረፋ መብዛትና በሲስተም መቆራረጥ የተነሳ የመታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት ተቸግረናል ሲሉ የአዲስ አባባ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ። የወሳኝ ኩነት አገልግሎት መቆራረጥን የሚቀርፍ ሲስተም እየለማ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አስታውቋል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ አያልነሽ ንጉሴ (ስማቸው የተለወጠ) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የነዋሪ መታወቂያ ለመውሰድ የሲስተም መቆራረጥ፤ ወረፋ፣ ወጥ የሆነ አሰራር ባለመኖሩ እና መስሪያ ቤቱ ለሙስና የተጋለጠ የአሰራር ሂደት የሚከተል ነው።

አገልግሎት አሰጣጡ የቀድሞ አሰራርን በማስቀረት በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ያሉት ወይዘሮ አያልነሽ፤ የተገልጋዩና አገልግሎት ሰጪው ቁጥር ባለመመጣጠኑ ረጅም ሰልፎች እንድንሰለፍ አድርጎናል። በዚህም በሥራዬ ላይ መስተጓጎል ፈጥሮብኛል ብለዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ነዋሪ አቶ ነጋሽ ማሞ (ስማቸው የተለወጠ) በበኩላቸው፣በወረዳው የመታወቂያ አሰጣጥ አገልግሎት ላይ መቸገራቸውን ተናግረዋል።



**አቶ ዮሴፍ ንጉሴ**

አቶ ነጋሽ የነዋሪነት መታወቂያ ለማግኘት ወደ ወረዳው የወሳኝ ኩነት ጽህፈት ቤት በተደጋጋሚ ቢያመሩም በወረዳው ቀልጣፋ፣ ምቹና ወጥ የሆነ አሰራር ባለመኖሩና ወረዳ መስሪያ ቤቱ ለሙስና የተጋለጠ የአሰራር ሂደት የሚከተል በመሆኑ በፈለጉት ጊዜ አገልግሎቱን እንዳላገኙ አብራርተዋል።

ዘመኑ የደረሰበትን የዲጂታል አሰራር በመጠቀም ስራቸውን እያከናወንን ነው ቢሉም የረቀቀውን ቴክኖሎጂ እየተጠቀሙ በአግባቡ ማገልገል አልቻሉም ሲሉ ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቀረቡትን ቅሬታዎች ይዞ ወደሚመለከታቸው አካላት ባደረገው ማጣራት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ የወሳኝ ኩነት ጽህፈት ቤት ኃላፊን እንደአጠቃላይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን አነጋግሯል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ የወሳኝ ኩነት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እልፍነሽ ጉዲታ በወረዳው የአገልግሎት ጥራት መጓደልን አስመልክቶ በሰጡት ምላሽ፤ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ የወረዳ አሥራ አራትና አሥራ አምስት የወሳኝ ኩነት ሥራን ጨምሮ እየሰራ ነው ብለዋል።

ይህም በወረዳው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተገልጋይ እንዲኖር ስለሚያደርግ ተገልጋዮች እንደየአመጣጣቸው የወሳኝ ኩነት አገልግሎት ያገኛሉ። ነገር ግን የሚያጋጥመውን እንግልት ለመቀነስ የወረዳው ሠራተኞች ከእሁድ እስከ እሁድ እየሰሩ ይገኛል ብለዋል።

ብዙ ቁጥር ያለውን ነዋሪ በሦስት ኮምፒውተር የወሳኝ ኩነት አገልግሎት እየሰጠን ነው ያሉት ወይዘሮ እልፍነሽ፤ ያለው ኮምፒውተር ከተገልጋዩ ቁጥር ጋር ባለመመጣጠኑ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ተቸግረናል ብለዋል።

ለአገልግሎት አሰጣጡና ለተገልጋዮች እንግልት እየፈጠረ ያለው የሲስተም መቆራረጥ ነው። ይህ ችግር በወረዳው የሚፈታ ሳይሆን በከተማ ደረጃ ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዮሴፍ ንጉሴ በአገልግሎቱ ላይ የሲስተም መቆራረጥ መኖሩን አምነው፤ ከወሳኝ ኩነት አገልግሎት ጋር ተያይዞ በመዲናዋ የሚያጋጥሙ የሲስተም መቆራረጥን የሚፈታ ሲስተም እየለማ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ዮሴፍ ገለፃ፤ በመዲናዋ ከወሳኝ ኩነት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የወረፋ መብዛትና የሲስተም መቆራረጥ ችግር እያጋጠመ ነው። የሲስተም መቆራረጥ እየተፈጠረ ያለው አገልግሎቱ ለአራት ወር ተቋርጦ ስለተጀመረ እና ለአገልግሎቱ የምንጠቀመው ሲስተም ለዚህ አላማ የሚውል ባለመሆኑ ነው። ነገር ግን አሁን ላይ ይህን ችግር የሚፈታ ሲስተም እየለማ ነው ብለዋል።

ይህ ሲስተም ወደ ሥራ ሲገባ ነዋሪዎች የሚያጋጥማቸውን እንግልት እንደሚቀርፍ እና የወሳኝ ኩነት ሰራተኞች አሰራር ቀልጣፋ እንደሚያደርግ የተናገሩት አቶ ዮሴፍ፤ ሲስተሙን በማልማት በኩል በቂ እውቀትና ችሎታ ያላቸው ድርጅቶችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል ብለዋል።



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

# የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎችን እያሰለጠነ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጠና ማዕከል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎችን እያሰለጠነ ነው።

በስልጠናው ተሳታፊ የሆኑት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብሮድካስት ማኔጅመንት ክፍል የቴክኒክና ፕሮዳክሽን ቡድን መሪ ጋዜጠኛ ሀብታሙ ብርሃኑ፤ ከዚህ ቀደም ስለጋዜጠኝነት እንጂ ስለሕዝብ ግንኙነት ስልጠና ወስጄ አላውቅም። ስለዚህ እንደ ሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ምን አይነት አጀንዳ እንደሚዘጋጅና ምን ምን ሂደቶች ማለፍ እንዳለበት ከስልጠናው የምረዳበት አጋጣሚ ይፈጥርልኛል ብሏል።

የስልጠናው ይዘት የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያን ብቁ ማድረግ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ለባለሙያዎች ወሳኝ ነው ያለው ጋዜጠኛ ሃብታሙ፤ ስልጠናው ለተግባር የሚያነሳሳና ቅርብ የሆነ ነው። ከዚህ ባለፈ በቆይታ የሚረሱ ጉዳዮችን ለማስታወስ ይረዳል ብሏል።

የስልጠናው ይዘት የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንዴት አጀንዳ መቀረጽ እንዳለበት የሚያሳውቅ መሆኑ ባለሙያው በሥራው ብቁ የሆነ እውቀትና ችሎታ እንዲኖረው እንደሚያደርግ ተናግሮ፤ ስልጠናው ሲጠናቀቅ የተሻለ ዕውቀት እንዲኖረኝ ያደርጋል ብሏል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የህትመት ዘርፍ ቡድን መሪ አቶ ተፈሪ ጋሞ በበኩሉ፤ ስልጠናው ከምሰራው ሥራ ጋር ግንኙነት ያለውና በምፈልገው ልክ የተዘጋጀ ስለሆነ፤ በሥራው ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች እንዲለይና እንዲስተካክል እንደሚያደርገው አስረድቷል።

በስልጠናው እንደኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ ብዙ የማላውቃቸውን እንዳውቅና ምን ማድረግ እንዳለብኝ እየተማርኩ ነው። ይህም በቀጣይ በተቋሜ ለምሰራቸው ሥራዎች ዝግጁና ውጤታማ እንድሆን ያደርገኛል። ስለዚህ ስልጠናው በጣም ጥሩ እና እኛን የሚመጥን ነው ብሏል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየተሰጠ ያለው ስልጠና የኮሚዩኒኬሽን ሥራ ላይ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ እና አቀራረቡ ሰልጣኙን የሚያሳትፍ መሆኑ ስልጠናው ማራኪ እንዲሆን አድርጎታል ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብሮድካስት ሚዲያ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ አዘነጋሽ ወልዴ ናቸው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከል በሕዝብ ግንኙነት በመገናኛ ብዙሃን በማስታወቂያና መሰል ዘርፎች በርካታ ተቋማትን ያሰለጠነ ሲሆን፤ በቅርቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጠውን ትልቅ የምርመራ ጋዜጠኝነት ስልጠናን ያካሄደ መሆኑም ይታወሳል።



ፎቶ - ገባቦ ሀብቴ

# በህዳሴ ግድብ ላይ ያተኮረ «መነሻ» የተሰኘ ዓለም አቀፍ የስዕል ሲምፖዚየም ሊካሄድ ነው

**- ባለፉት ስድስት ወራት ለግድቡ ከ867 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በህዳሴ ግድብ ላይ ያተኮረ ዓለም አቀፍ የስዕል ሲምፖዚየም ከጥር 18 እስከ ጥር 27 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚካሄድ የግድቡ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የግድቡ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ግድቡ መላው ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና አሻራቸውን እያሳረፉበት ያለ ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው። በዚህም ባለፉት ዓመታት ግድቡ ላይ ያተኮሩ በርካታ የኪነጥበብና ሥነጥበብ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ከሰሞኑም ከጥር 18 ጀምሮ ለ10 ቀናት የሚቆይ “መነሻ” በሚል መሪ ቃል የተሰየመውና በባህር ዳር እና አዲስ አበባ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ የስዕል ሲምፖዚየምም ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ታዋቂ ሰዓሊያን የሚሳተፉበት ስለሆነ ለሀገራዊ ገጽታ ግንባታና ለሕዝባዊ ዲፕሎማሲ መጠናከር ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን ለግድቡ ግንባታ የሚያደርጉት ሁለንተናዊ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠሉን አመልክተው፤ ባለፉት ስድስት ወራት ከ867 ሚሊዮን 920 ሺህ ብር በላይ ገንዘብ መሰብሰቡን ጠቅሰዋል። በቀጣይነትም ሕዝቡ ይህን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ጋር በመተባበር ሲምፖዚየሙን ያዘጋጀው ሰዓሊ ታምራት ሱልጣን በበኩሉ፤ ሲምፖዚየሙ ኢትዮጵያ የዓባይ ወንዝ መነሻ መሆኗን ለዓለም ለማሳወቅና ግድቡም የተፋሰሱን ሀገራት ጭምር ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ለማሳየት ያለመ ነው ብሏል።

በሲምፖዚየሙ ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ 25 ሰዓሊያን እንደሚሳተፉ ጠቅሶ፤ ሰዓሊያን ወደ ባህርዳር አቅንተው ለሁለት ቀናት የዓባይን ወንዝ መነሻና ያለውን ሀሳብ ከቃኙ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በተዘጋጀላቸው ጀልባ ላይ የስዕል ሥራዎቻቸውን እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

መርሃ ግብሩ ሥነ ጥበብ ያለውን ታላቅ አቅም ተጠቅሞ ሕዝባዊ ዲፕሎማሲን በማጠናከር በኩል ትልቅ ሚና እንደሚጫወትም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሰርጸ ፍሬስብሐት እንደገለጹት ደግሞ፤ በቀደሙት ዓመታት የኪነጥበብ፣ የስነጽሑፍና ስነጥበብ ሥራዎቻችን የዓባይን ሁኔታ በቁጭት ሲገልጹት ኖረዋል።

ከቁጭት ተሻግረን ዛሬ ላይ ስንደርስም ደስታችንን ለመግለጽ የተጠቀምነው እነዚህን ጥበባዊ ሥራዎች ነው ብለዋል።

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የጥበባዊ ሥራዎችን አቅም ተገንዝቦ ሲደግፍ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በቅርቡ የሚደረገውን ዓለም አቀፋዊ የስዕል ሲምፖዚየም አስፈላጊውን ድጋፍ ስላደረገም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ 17 ቢሊየን 650 ሚሊዮን ብር አጠቃላይ ድጋፍ ማድረጋቸው የተጠቆመ ሲሆን፤ ይህንን ድጋፍ በቀጣይነትም አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ ቀርቧል።



አቶ ያዕቆብ ሸራተን

## በጋምቤላ ክልል ማጃንግ ዞን በሙስና የተጠረጠሩ 14 አመራሮችና ግለሰቦች ላይ ክስ ተመሰረተ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በሙስና ድርጊት የተጠረጠሩ 14 አመራሮችና ግለሰቦች ላይ ክስ መመስረቱን በጋምቤላ ክልል የማጃንግ ዞን ፍትህ መምሪያ ገለፀ።

የማጃንግ ዞን ፍትህ መምሪያ ኃላፊ አቶ ያዕቆብ ሸራተን እንደገለፁት፤ ከሙስና ድርጊት ጋር ተያይዞ ከተጠረጠሩት 14 ግለሰቦች ውስጥ ስድስት ግለሰቦች በዋስ ተለቀው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ እየተደረገ ይገኛል። የተቀሩት ስምንት ግለሰቦች ደግሞ የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸው ማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

ርምጃው የተወሰደው በጋምቤላ ክልል ከሚከናወን የመንገድ ግንባታ የመሬት ካሳ ጋር በተያያዘ በደረሰ ጥቆማና የማጣራት ስራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በጋምቤላ ክልል ከአቦቦ እስከ ኩቢጦ ማዞሪያ የሚሰራው የመንገድ ስራ ተቋራጭ ድርጅት በአካባቢው ካምፕና የድንጋይ መፍጫ የሰራበት ቦታ ላይ ግምት አልተከፈለንም በሚል የአካባቢው ነዋሪዎች ለመንግስት ቅሬታ በማቅረባቸው ጉዳዩን የማጣራት ስራ ሲከናወን እንደቆየ አቶ ያዕቆብ ገልጸዋል።

ጉዳዩን በማጣራቱ ሒደት ከቀበሌ እስከ ዞን ያሉ ጥቂት አመራሮች የግል ጥቅም በመፈለግ የግለሰቦቹን የይዞታ ግምት በተጭበረበረ መልክ የተከፋፈሉ ስለመሆናቸው ከባንክ ጭምር የተገኙ ሰነዶች እንደተገኙ የፍትህ መምሪያ ኃላፊው አስታውቀዋል።

በድርጊቱ ተሳታፊ የሆኑት ከማጃንግ ዞን አንድ ከፍተኛ አመራርና አንድ የፖሊስ የስራ ኃላፊ ፣ ከጎደሬ ወረዳ አንድ ከፍተኛ አመራር ፣ከመንገሺ ወረዳ ሶስት በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሲሰሩ የነበሩ ግለሰቦች እንዲሁም የቀበሌ አመራሮችና ሌሎችም ተባባሪዎች ከስራቸው ታግደዋል። ጉዳያቸውም በፍርድ ቤት የምርመራ መዝገብ ተከፍቶ በመጣራት ላይ ይገኛል ብለዋል።

የማጭበርበር ድርጊቱ የተፈፀመው በአንድ ቀበሌ በመሆኑ ድርጊቱን ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች በሕግ እንዲጠየቁ ሲደረግ፤ በመንገድ ስራው ላይ የሚያስከትለው የከፋ መስተጓጎል የለም ያሉት አቶ ያዕቆብ፤ ጉዳዩ ከግለሰቦች ጋር ብቻ የተያያዘ መሆኑንና ከግንባታው ስራው መቀጠልና አለመቀጠል ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ ሊታወቅ ይገባል ብለዋል።

አቶ ያዕቆብ አክለውም፤ የክልሉ መንግስት በየትኛውም አግባብ ሙሰኞችና የግል ጥቅም አሳዳጆችን የማይታገስ መሆኑን ህዝቡ ተረድቶ ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል። ጥፋተኞችን በማጋለጥም ረገድ ህብረተሰቡ በክልል ለተቋቋመው የጸረሙስና ኮሚቴና በየዞኑ ለሚገኙ ፍትህ ቢሮዎች መረጃዎችን ማድረስ ይገባዋል።

መንግስትም በሚደርሰው መረጃና ማስረጃ መሰረት በአመራርነትም ሆነ በታችኛው የስራ ደረጃ ላይ የሚገኙ ግለሰቦችን ተጠያቂ እንደሚያደርግ አቶ ያዕቆብ አሳስበዋል።

## በመዲናዋ ተገጣጣሚ ቤቶችን ለመገንባት 30 ህንፃ ተቋራጮች እየተሳተፉ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታን ለመገንባት 30 ህንጻ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተሳተፉ መሆኑን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ቅርንጫፍ 10 ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ አቶ በየነ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለተገጣጣሚ ቤቶቹ ግንባታ የሚውል ግብአቶች በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የሚመረት ሲሆን፤ በግንባታ ስራው ከ30 በላይ ኮንትራክተሮች እየተሳተፉ ይገኛል።

በተገጣጣሚ ቤቶቹ ግንባታ ከተቋራጮቹ ባለፈ በስራቸው ተቀጥረው ለሚሰሩ ሰራተኞች የስራ እድል እንደፈጠረ የተናገሩት ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ፤ ከስራ ዕድል ፈጠራው ባለፈ በተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ዘርፍ የዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ለማስተላለፍ የሚያስችል ዕድል መፈጠሩን ገልጸዋል።

በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚከናወነው የተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ከዚህ በፊት ከነበረው የቤት አሰራር ግንባታ ስራ በተለየ በቴክኖሎጂ ታግዞ በአነስተኛ ወጪና ጊዜ ውስጥ የግንባታ ሂደቱን ማጠናቀቅ የሚያስችል ነው ብለዋል።

አቶ በየነ እንደገለጹት፤ ከመሬት በላይ ባለአራት ወለል ያላቸው ሰባ ህንጻዎችን በተገጣጣሚ ቤቶች ቴክኖሎጂ ታግዞ ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል። ባለፉት ስድስት ወራት የ2ሺ 318 ቤቶች ግንባታ ተከናውኗል።

ከዚህ በተጨማሪ ከመሬት በላይ ባለ ዘጠኝ ወለል 20 ህንጻዎች ግንባታቸው እንደሚከናወን የተናገሩት የፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ፤ በቴክኒካል ጉዳዮች ምክንያት እና በፈቃድ መዘግየት ምክንያት የተጓተተው ስራ በቀጣይ እንደሚጀመር ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነባ ያለው የቃሊቲ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ በተያዘለት የ18 ወራት የግንባታ ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከሚመለከታቸው አጋር አካላቶች ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የወሰን ማስከበር፣ የግንባታ አቅርቦት እጥረት በተለይም የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት ፣የገበያ ዋጋ ንረት እና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች ባለፉት ወራት ስራው በተፈለገው ፍጥነት እንዳይሄድ አግደው እንደነበር አስታውሰዋል።

አሁን ላይ የሲሚንቶ አቅርቦት ላይ የነበረው ችግር እየቀነሰ ቢሆንም በዘላቂነት ችግሩን ለመፍታት ከፋብሪካዎች ጋር በቀጥታ ግንኙነት በመደረግ ላይ ነው።

የወሰን ማስከበር ችግሮችን ለመፍታትም ከክፍለ ከተማ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በመሆን እየተሰራ ነው ብለዋል።

እንደ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ገለፃ፤ የተገጣጣሚ ቤቶቹ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ በዝቅተኛ እና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚተላለፉ ይሆናል።

በመጀመሪያው ዙር የሚገነቡት አምስት ሺ የተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታቸው የተጀመረው ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም ላይ ነበር። በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለተገጣጣሚ ቤቶቹ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ስምንት ቢሊየን ብር መመደቡን ማስታወቃቸው የሚታወስ ነው።



## በደቡብ ክልል ከ700 ሺህ ሄክታር በላይ የተፋሰስ ልማት ተጀምሯል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት በተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ከ700 ሺህ ሄክታር በላይ ለማልማት በመስራት ላይ እንደሚገኝ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ልማቱ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞችና ጠረጴዛማ እርከንን ማዕከል በማድረግ ከትናንት ጀምሮ ለ35 ቀናት ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪ እና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡሱማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራ "ተፈጥሮ ሀብታችን ለሁለንተናዊ ብልፅግናችን" በሚል መሪ ቃል ተግባራዊ ይደረጋል።

ተግባራዊ መደረግ የጀመረው የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር አምስት በመቶ ጭማሪ አለው ያሉት ኃላፊው፤ እንደ ክልል በሀላባ ዞን ወይራ ዲቾ ቁሊቶ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ቀበሌዎች የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በይፋ ተጀምሯል።

እንደ አቶ ኡሱማን ገለጻ፤ ልማቱ እስከ አሁን ድረስ የነበሩ ልምዶችን መሰረት በማድረግ የዘንድሮው በተለየ መንገድ ተግባራዊ ይደረጋል። አዳዲስ እርከኖችን ሰርቶ ማልማት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት የተሰሩ እርከኖች እድሳትና ጥገና ይካሄዳል። አረንጓዴ አሻራ፣ የሌማት ቱሩፋቶች፣ ከጥምር ደን እና ከመስኖ ልማት ጋር በማስተሳሰር ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ላይ ትኩረት በማድረግም ተግባራዊ ይደረጋል።

በተለይ ከጉራጌ ተራሮች ስር ተነስተው ስልጤ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ እና ወላይታ ዞኖችን እንዲሁም የኦሮሚያ ክልልን በማቋረጥ እስከ ብላቴ ድረስ በሚጓዙ ወንዞች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል ያሉት አቶ ኡስማን፤ ተሞክሮውን ለሌሎች በማጋራት ክልላዊና ሀገራዊ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

እስከ አሁን ድረስ በተሰሩ የተፋሰስ ልማት ስራዎች ዘጠና ስድስት በመቶውን ማሳካት ተችሏል ያሉት አቶ ኡስማን፤ ከዚህም የተነሳ ተጨባጭ ውጤት በመታየት ላይ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ ከዚህ ቀደም በተሠሩ ሥራዎች በርካታ የተጎዱ መሬቶች አገግመው ወደ ልማት ገብተዋል። የከርሰ ምድር ውሃ ከተራሮች ስር በመፍለቅ ለመስኖ እርሻ ተጨማሪ መሬት ማግኘት ተችሏል። የአፈር ለምነት እየጨመረ በመሆኑ በተጎዱ አካባቢዎች ወጣቶች የእንስሳት መኖ በማምረት ገቢ ማግኘት ጀምረዋል።

በመሆኑም የዘንድሮ የተቀናጀ ልማት ተፋሰስ ስራ ከአረንጓዴ አሻራ ልማት፣ ጥምር ግብርና እና ከሌማት ትሩፋቶች ጋር ከማስተሳሰር ጎን ለጎን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን አትክልት እና ፍራፍሬዎች፣ ቀርከሃ፣ ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ እና የቡና ችግኞችን ጨምሮ 750 ሺህ ችግኞችን በተጎዱ አካባቢዎች ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በፈተና ውስጥ ገዝፎ አገርን የማሻገር ጉዞ ማሳያ!

ወርቅ ከአፈር ተለይቶ ወርቅ የሆነው በእሳት ተፈትኖ አንጸባራቂ ገጽታን በመላበሱ ነው። ይህ በእሳት ውስጥ አልፎ የፈጠረው አንጸባራቂነቱ ደግሞ ለስሙ ግዝፈትም ከፍ ላለው ዋጋውም ምክንያት ሆኖታል። ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ ናቸው። ከፍ ያለ ታሪካቸው፣ ያልተቆራረጠ ሥርዓተ መንግስታቸው፣ የሰብዕና ልዕልናቸው፣ ወኔና አልበገር ባይነታቸው፣ ኅብረትና አሸናፊነታቸው እንደ ወርቅ በዘመናት እሳት ተፈትነው የገነቡት ልዕልናቸው ነው። ሆኖም በየዘመኑ በሚገጥሟቸው ፈተናዎች መውጣት መውረዳቸው፤ አልፎ አልፎም በፈተናዎቹ ተደነቃቅፈው መንገዳገዳቸው የማይካድ ሃቅ ነው።

ይሄን የመንገዳገድ ታሪክ ከመቀየር አኳያ ደግሞ በየዘመናቱ የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም፤ ከ2010ሩ አገራዊ ለውጥ በኋላ የተከናወኑ ተግባራት ግን ለችግሮቹ መፍትሄ ይዘው ስለመምጣታቸው መገንዘብ ይቻላል። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ የለውጥ ማግስት የሪፎርም ስራዎችና ውጤቶቻቸው ሲሆኑ፤ በተለይ የጸጥታ፣ የደህንነት እና የፍትህ ተቋማት ላይ የተደረገው ጥልቅና ምሳሌያዊ የሆነ ማሻሻያ ተጠቃሾች ናቸው።

አገር እንደ አገር ሉዓላዊነቷ ተጠብቆና ተከብራ እንድትኖር፤ ሕዝብም እንደ ሕዝብ የደህንነት ስጋት ሳይኖርበት ሙሉ አቅምና ትኩረቱን በልማት ስራዎች ላይ እንዲያውል ከፍ ያለውን ሚና የሚወጡት የፀጥታ ተቋማት ላይ የተደረገው ሪፎርም ከዕለት ዕለት ከፍ እያለና የኢትዮጵያን የከፍታ ግስጋሴ ልክ እያመላከተ የሚገኝ መሆኑ ነው። በዚህ ረገድ ከለውጡ ማግስት በመከላከያ እና ፌዴራል ፖሊስ ላይ የተደረገው ጥንቃቄ የተሞላበት ሪፎርም፤ ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት የገጠሟትን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች በድል እንድትወጣ አድርጓል።

በተለይ በመከላከያው ዘርፍ የተሰራው የሪፎርም ሥራ ኢትዮጵያ በውስጥም ሆነ በውጪ ጠላቶቿ የተቃጣባትን አደጋ በብቃት እንድትመክት እና ጥላቶቿን አሳፍራ ሉዓላዊነቷን አስከብራ እንድትሻገር ያደረገ ነው። በኔትዎርክ ተጠልፎ አገራዊ ወኔ እንዲርቀው ተደርጎ የተሰራበትን ተቋም ወደ ኃያልነትና አሸናፊነት ማንነቱ እንዲመለስ፤ ከሜካናይዝድ፣ ከአየር ኃይል፣ ከባህር ኃይል፣ ከቴክኖሎጂና መሰል የጦር ኃይሎች ተነጥሎ እና በአቅም ተዳክሞ እንዲገለጥ የተፈረደበትን ተቋም ሁሉን አቀፍ ኃይል ፈጥሮና በቴክኖሎጂ ተደግፎ፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂውን አውቆ በሚጠቀም የሰው ኃይል ተደራጅቶ በድል ላይ ድል እንዲጎናጸፍ ማድረግ ተችሏል።

ከሁለት ዓመታት ፈታኝ የጦርነት ውሎው ማግስት ከሰሞኑ የተገለጠው እውነትም የዚህ አንድ ማሳያ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያም በፈተናዎች ውስጥ የምትበረታ፣ በችግር ውስጥ የተሻለ እድል መፍጠር የምትችል፣ በጦርነት ውስጥም ሆና የመሻገሪያ አቅም የምትገነባ ታላቅ አገር መሆኗን ያረጋገጠችበት ነው። ምክንያቱም ሰሞኑን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ እና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ ሌሎች የጦር ከፍተኛ አዛዦች በተገኙበት የታየው የኢትዮጵያ የጦር አቅም፤ ኢትዮጵያ ወደፊት ሊቃጡባት የሚችሉ ጥቃቶችን የመመከትና በድል የማጠናቀቅ አቅም ብቻ ሳይሆን፤ ጥቃት ለመፈጸም ያሰቡ ኃይሎች ቆም ብለው ደጋግመው እንዲያስቡ እና ካልተገባ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ የሚያደርግ ነው።

ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ አገር ልታሳካው እየተጋች ላለችበት የብልጽግና ጉዞ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የሁሉም ነገር መሰረቱም፣ ማሰሪያውም ሰላም ነውና። ሰላም ደግሞ ስለፈለጉትና ስላወሩለት የሚመጣ አይደለም። አንዳንዴም ሰላምን ለማደፍረስ የሚሻ ኃይል ቢነሳ እንኳን አደብ ማስያዝና ያሰበውን ሳያፈጽም ማስቀረት እንደሚቻል አቅም መኖሩን ማሳየት መቻል የግድ ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ላለፉት ዓመታት በፈተና ውስጥ ያሳለፈች ቢሆንም፤ በአንድ በኩል ሰላሟን ለማረጋገጥ እየሰራች፤ በሌላ በኩል በተገኘው ፋታ የልማት ተግባራትን ሳታቋርጥ ዘልቃለች። ለሰላሟ መሰረት፣ ለልማቷም አጋዥ የሚሆናትን የሰላም አስከባሪና አጽኚ ኃይልም ገንብታለች።

ይሄ ደግሞ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ ሂደት ውስጥ የማድረግ አቅም ያለው ኃይል የመፍጠር ዋናው ርምጃ ነው። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሉ እንደነበረውም፤ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ እና ሌሎችም የደህንነት ተቋማት እጅግ ዘመናዊ በሆነ መንገድ የማድረግ አቅም፤ ውጊያን የማስቀረት አቅም፤ ውጊያም ሲጀመር በአጭር የመቋጨት አቅም ያላቸውን ኃይሎች እውን ለማድረግ ተሰርቷል። የዚህ ሥራ ዋነኛ ዓላማም ጠንካራ፣ የማይደፈር እና በቀላሉ የማይቆረጥም ኃይል ሲኖር ጠላት ውጊያን ደጋግሞ እንዲያስብ እና እንዲያስቀር ስለሚያደርግ ነው። ይሄ እውን የሚሆነው ደግሞ የጦር ክንፎች (አየር ኃይል፣ ሜካናይዝድ፣ እግረኛው እና ሌላውም ምድብተኛ) ተናብበው እና በቴክኖሎጂ ታግዘው መስዋዕትነትንና ኪሳራን በመቀነስ በአጭር ጊዜ የሚፈለገውን ድል ማሳካት ሲችሉ ነው።

በዚህ መልኩ የጠነከረ ኃይል መገንባት እና ይዞ መገኘት ደግሞ ለኢትዮጵያ ጸንቶ መቆም ድርሻው ተኪ የሌለው ነው። ከዚህም በላይ የእነዚህ ኃይሎች ከፍ ያለ ልዕልናን መላበስና መያዝ ኢትዮጵያ ልታሳካ ያሰበችውን ልማት እውን እንድታደርግ ምቹ መደላድልን ይፈጥራል። በሌላ ገጹም የኢትዮጵያ የልማት ምንጭም ድልድይም ሆኖ የሚያገለግል ነው። አለፍ ሲልም እንደ ወርቅ ተፈትኖ በተፈጠረ አቅም እና በተገነባ ልዕልና ውስጥ አገርን ከፍ የማድረግ፤ ወደ ሁለንተናዊ ብልጽግናዋ ድልድይ ሆኖ የማሻገር ድንቅ የተግባር ጉዞ ማረጋገጫም ሕያው ምስክር ነው።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአዋሽ አርባ ውጊያ ትምህርት ቤት ተገኝተው በአየር ኃይል እና በሜካናይዝድ ቅንጅት የተካሄደውን የጥምር ጦር ወታደራዊ ትርዒት አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት፤

# «ጠንካራ ኃይል፣ የማይደፈር ኃይል፣ በቀላሉ የማይቆረጠም ኃይል ሲኖር ጠላት ውጊያን ደግሞ እንዲያስብና እንዲያስቀር ያስገድዳል፤»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከትናንት በስቲያ በአዋሽ አርባ ውጊያ ትምህርት ቤት ተገኝተው በአየር ኃይል እና በሜካናይዝድ ቅንጅት የተካሄደውን የጥምር ጦር ወታደራዊ ትርዒት ተመልክተዋል። በአዋሽ አርባ ውጊያ ቴክኒክ ትምህርት ቤት በመቀጠልም በቢሾፍቱ የሚገኘውን የአየር ኃይል ዋና መምሪያ በመገኘት በዝግጁነት ላይ የሚደረገውን ማሻሻያ ጎብኝተዋል። ምልከታ እና ጉብኝታቸውን መነሻ በማድረግም "ጠንካራ ኃይል፣ የማይደፈር ኃይል፣ በቀላሉ የማይቆረጠም ኃይል ሲኖር ጠላት ውጊያን ደግሞ እንዲያስብ እና እንዲያስቀር ያስገድዳል፤" ያሉ ሲሆን፤ ይሄን ያስደመጡበት ንግግራቸው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ ጄነራል አበባው ታደሰ፣ ኮምሽነር ጄነራል ደመላሽ፣ የአየር ኃይል አዛዥ፣ መድፈኛ አዛዥ የተከበራችሁ ጄነራሎች፣ የጦር ሰራዊት አባላት በዚህ በሚያምር መስክ ለሀገር ኩራት የሆኑ እና ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ በክብር እንድትኖር ጋሻ መከታ ለመሆን የሚችለውን ኃይል ለማየት በመታደሌ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ።

በኢትዮጵያ የጀመርነው ሪፎርም ከዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ቀጥሎ አበክረን ስንሰራበት የነበረው የኢትዮጵያን ኮርቼቭ ፓወር የማድረግ አቅም ያለው ኃይል ግንባታ ነው። በዚህ ግንባታ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የደህንነት ተቋማት፣ እጅግ ዘመናዊ በሆነ መንገድ እስካሁን በኢትዮጵያ ታሪክ ተገንብቶ በማይታወቅ ልክ እነዚህን የማድረግ አቅም፣ ውጊያ የማስቀረት አቅም ፣ ውጊያ ሲጀመር በአጭር የመቅጨት አቅም ያላቸውን ኃይሎች ላለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት በከፍተኛ ትኩረት ስንሰራ ቆይተናል።

ይሄ ኮርቼቭ ፓወር /ኃይል ግንባታ የሚያስፈልግበት ዋነኛው ዓላማ፡- አንደኛው ውጊያ ለማስቀረት ነው። ጠንካራኃይል፣የማይደፈርኃይል፣በቀላሉየማይቆረጠም ኃይል ሲኖር ጠላት ውጊያን ደግሞ እንዲያስብ እና እንዲያስቀር ያስገድዳል፤ ዲተር የማድረግ ኃይል አለው። ሁለተኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ላለፉት በርከት ላሉ አስርት ዓመታት የነበረን የውጊያ ስርዓት ይሄን ወደ ዘመናዊ የውጊያ ስልት ለመቀየር ያለው ዋነኛው መንገድ የአየር ኃይል እና የከባድ መሳሪያ አቅምን ማጠናከር ብቻ ሳይሆን መቀናጀት ነው። አየር ኃይል እና መድፈኞች፣ ታንከኞች፣ መድፈኞች፣ ሚሳኤል ምድብተኞች፣ ውጊያን ይጀምራሉ፣ ውጊያን ያጧጡፋሉ፤ አስፈላጊ ሲሆን ትጥቅ ኤልት ፎርስ እስፔሻል ፎርስ ውጊያን ይጨርሳል። የሰው መስዋትነት ቀንሰን በመሳሪያ ኃይል በቴክኖሎጂ ኃይል ውጊያን ጀምረን እንድንጨርስ መስዋትነት እንድንቀንስ ያስቀመጥነውን ግብ የሚያሳካው ትልቁ ስራችን እና ውጤቱ በሁሉም ዘርፍ ያሉ የከባድ መሳሪያ አቅሞቻችን ከአየር ኃይል ጋር ተቀናጅተው እየተናበቡ ለውጊያ ዝግጁ መሆናቸው ነው።

የተከበረው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና በውስጡ የምትገኙ የጦር መኮንኖች እና የሠራዊት አባላት ኢትዮጵያ ፀንታ እንድትቆም የናንተ መጠንከር፣ የናንተ ብቁ መሆን ሁልጊዜም ለባንዲራ እና ለመለዮ የማይዛነፍ አቋም ያለው ኃይል መሆን የምናስበውን ልማት እንዲፋጠን ያደርጋል። ሁላችሁም እንደምታውቁት ያደግንበት ቤት ስለሆነ ኢትዮጵያ አሁን ባላት ልክ የአየር ኃይል፣ የካባድ መሳሪያ የመዋጋት አቅም፣ ክላሽ የመጠገን አቅም በሠራዊት ቁጥር እና በጦር መኮንኖቻችን በወረቀት ላይ ሳይሆን በውጊያ የተፈተነ ብቃት ኖሮን አያውቅም፤ ከፍተኛ ኃይል ተገንብቷል።

ይህ ኃይል ለኢትዮጵያ የልማት ምንጭ እና ድልድይ ሆኖ እንዲያገለግል፡- አንደኛ በዚህ ስፍራ ያየነው የጦር ልምምድ ማሳያ ቦታ በሚቀጥለው ጊዜ ስንገናኝ እጅግ ተውቦ በርከት ያሉ ሲቪሊያንስ መጥተው የሚያዩበት ሰፈር እንዲሆን፤ ይሄንን ቦታ የምንሰለጥንበት ወጣ ብለን የምንዝናናበት፣ ኃላፊዎች ከከተማ እየመጡ ከናንተ ጋር የሚገናኙበት ውብ ስፍራ ማድረግ ስለምንችል፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤቱን እጅግ ዘመናዊ አድርጎ በአፍሪካ ውብ ስፍራ ማድረግ ችሏል። የአየር ኃይሉንም እንደዛው በጣም በተዋበ መንገድ መቀየር ተችሏል፤ ይሄንን ስፍራ ቀይረን መከላከያ የብልፅግና ምልክት፣ የዕድገት ምልክት፣ የቴክኖሎጂ ምልክት እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው የፖለቲካ ሽቀጥ፣ የፖለቲካ ገበያ፣ ዘረኝነት፣ በእምነት በአካባቢ መከፋፈል ላይ ያጠነጠነ ነው። ከኢትዮጵያዊነት አንድ ደረጃ ዝቅ ስትል ውርደት፣ ዝቅ ስትል መፍረስ፣ ዝቅ ስትል መበተን መሆኑን በተግባር ያየን ስለሆንን፤ ከከፍታቹ ዝቅ ሳትሉ አንድ መሆናችሁን በተግባርም እያጠናከራችሁ ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ፣ ማልማት፣ መጠበቅ እና ለልጆቻችን ማሸጋገር ህይወት ዘመን ተልዕኳችሁ መሆኑን ተገንዝባችሁ፤ የውስጥ አንድነት እንድታረጋግጡ አበክራችሁም እንድትሰሩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

አሁን ባለው ዘመን የሶሻል ሚድያው ዋናው ስራው በሰፈር፣ በእምነት፣ በዘር ብቻ ሳይሆን በትንንሽ ወረዳዎች የመከፋፈል አባዜ ነው። ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያን ያሳንሳል። ትልቅ ሀገር ነው ያለን ፣ ሊለማ የሚችል ሀገር ነው ያለን፣ ሰፊ ህዝብ ነው ያለን አንድ መሆን ከቻልን ሌሎችን መሳብ የምንችል እንሆናለን፤ ስንለያይ ስንበተን ግን ለጠላት ለጥቃት የምንጋለጥ ስለምንሆን በዚህ ልክ ጠንካራ መሆን ዘመናዊ ትጥቅ መታጠቅ ብቻ ሳይሆን የውስጥ አንድነት እና ወንድማማችነትን ማጠናከር ከሁላችሁም የሚጠበቅ የዕለት ተዕለት ተግባር እንደሆነ ከአደራ ጭምር ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

በተደጋጋሚ እንዳነሳሁት ኢትዮጵያን የድህነት ታሪኳን ቀይረን አንድ መሆኗን ለእኛም ለዓለምም አሳይተን የምናሻግራት ዕንቁ ምድር እንጂ የምትበተን በጎጠኞች፣ በፅንፈኞች፣ በአሸባሪ ኃይሎች፣ የምትለያይ ሀገር አለመሆኗን በተደጋጋሚ ተናግረን በተግባርም ማሳየት እንደቻልነው ሁሉ፤ በሚቀጥሉት ዘመናት በልማት ጠንክረን በሰላም ጠንክረን ውጊያ በሚያስቀር አቅም ጠንክረን የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቀን ሰላማችን እና ልማታችንን አረጋግጠን ልጆቻችን የበለፀጉ የለሙ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ሀገራቸውን የሚወዱ በሀገራቸው የሚሰሩ የማይሰደዱ እንዲሆኑ ለኛ ትውልድ የተጣለ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን በጋራ እንድንሰራ አደራ እያልኩ፤ ዛሬ ባየሁት ብቃት፣ ዛሬ ባየሁት ልምምድ፣ ዛሬ ባየሁት ትርኢት እጅግ የኮራሁ መሆኔንና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይሄን የማየት ዕድል ሲኖረው በናንተ በልጆቹ ደግሞ ኩራቱን የሚያረጋግጥ እንደሚሆን ያለኝን ሙሉ ዕምነት እየገለፅኩ፤ እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን በርቱ የኢትዮጵያ ልማት እና ሰላም እንዲሁም አንድነት በእኛ አንድነት እና ጥንካሬ የሚረጋገጥ ይሆናል፤ ይሄን በጋራ ለማየት እንዲያበቃን እመኛለሁ። አመሰግናለሁ።

# በ1444ኛው ሐጅና ዑምራ እስከ 20 ሺህ ተጓዦች ለማሳተፍ ከስምምነት ተደረሰ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በ1444ኛው የሐጅና ዑምራ ሐጂ ተጓዦችን (ሑጃጆችን) ቁጥር እስከ 20 ሺህ ለማሳደግ ከሳውዲ አረቢያ መንግስት ጋር ከስምምነት መደረሱን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አስታወቀ። በሼህ አብዱልአዚዝ አብዱልወሊ የተመራው ልዑክ የሳውዲ አረቢያ ቆይታውን አጠናቆ ተመልሷል።



ሼህ አብዱልአዚዝ አብዱልወሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የዘንድሮውን የሐጅና ዑምራ ጉዞ ተሳታፊዎችን ቁጥር በማሳደግ ዙሪያ ለመምከር ወደ ሳኡዲ አረቢያ አቅንቶ የነበረው በእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት በሼህ አብዱልአዚዝ የተመራው ልዑክ የሳውዲ አረቢያ ቆይታውን አጠናቆ ተመልሷል።

ልዑኩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በ1444ኛው የሐጅና ዑምራ ሑጃጆችን (ሐጂ ተጓዦችን) ቁጥር እስከ 20 ሺህ ለማሳደግ ከሳውዲ አረቢያ ጋር ስምምነት ላይ ስምምነት ተደርሷል።

ልዑኩ በሳውዲ አረቢያ የሐጅ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በተዘጋጀው የ1444ኛው የሐጅ ኤክስፖ ከመላው ዓለም ከተውጣጡ የጉባዔው ተሳታፊዎች ጋር ኢትዮጵያን በመወከል ተሳታፊ ሆኗል።

በሐጅና ዑምራ መስተንግዶ ከፍተኛ ሑጃጆችን ከሚያስተናግዱ ሀገራት እንደ ማሌዥያ ካሉ ሀገራትና ከአፍሪካ ሀገራት ደግሞ የተሻለ መስተንግዶ ከሚሰጡ ከታንዛኒያ፣ ከሶማሊያ እና ከኬንያ ተሞክሮ መቅሰም መቻሉን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከናይጄሪያ ቀጥሎ ሰፊ የሑጃጅ ቁጥር የመጠቀም እድል ቢኖራትም በተለያዩ ምክንያቶች መጠቀም አለመቻሉን የገለፁት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ በዘንድሮ ዓመት የዕድሉ ተጠቃሚ ለመሆን ከሳውዲ የሐጅ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ጋር ሰፊ ውይይት አድርገናል ብለዋል። ከሳውዲ አረቢያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የሐጅና ዑምራ ምክትል ኃላፊ ከዶክተር አብዱል ፈታ ሱለይማን ጋርም የሐጅና ዑምራ ጉዳይ የማስተባበርና የአፈፃፀም ውል መፈረም መቻሉን ተናግረዋል።

ልዑኩ ጂዳ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንፅላ ጽህፈት ቤት ጋር ውይይት ያደረገ ሲሆን ከአሁን በፊት ሑጃጆች እንግልት ይደርስባቸው እንደነበር ያወሱት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ይህ ችግር እንዳይደገም እና ዜጎች ተገቢውን መስተንግዶ ማግኘት እንዲችሉ የቆንፅላ ጽህፈት ቤቱ ከጠቅላይ ምክር ቤቱ ጋር አብሮ እንደሚሰራ ገልጸዋል። በዘንድሮ ዓመት ለሐጅ ተጓዦች የሚሠጠው አገልግሎት ፈጣን፣ ግልፅና ከአላስፈላጊ እንግልት የፀዳ እንዲሆንም ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ምክር ቤቱ ለእምነቱ ተከታዮች የማገልገል ኃላፊነቱን ለመወጣት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እየሰራ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዝዳንቱ፤ በመካ በመዲና ለሑጃጁ አገልግሎት የሚሰጡ የሆቴልና የምግብ ሰጪ ድርጅቶች የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እየሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል።

የዘንድሮ የሐጅ መስተንግዶ የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የአውሮፕላን የቲኬት ዋጋ ለማወቅ ከአየር መንገዶች ጋር በቀጥታ ለመነጋገር በጠቅላይ ምክር ቤቱ ዕቅድ መያዙን ምክትል ፕሬዚዳንቱ የተገለጹ ሲሆን፣ በሀገር ውስጥና በሳውዲ አረቢያ የሚደረገው የቅድመ ዝግጅት ስራ እንደተጠናቀቀ ዝርዝር መግለጫ እንደሚሰጥ አመላክተዋል።

# «በሀገራዊ ምክክሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጥያቄዎች እንደነበሯቸውም ነው የተናገሩት።

በሂደት በተሰሩ ስራዎች ከ53ቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ከ40 በላይ የሚሆኑት አብረዋቸው ለመስራት የተስማሙ ሲሆን፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥም የስምምነት ማዕቀፍ የሚፈራረሙ መሆኑን ገልጸዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ አብሮ ለመስራት ፍላጎት ካላሳዩት ከአስር የሚልቁ ፓርቲዎች ጋርም አብሮ ለመስራት ጥረቶች መቀጠላቸውንም ተናግረዋል።

አብረውን ለመስራት ፍቃደኛ ካልሆኑት ፓርቲዎች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እየተገናኘን እኛ ማን እንደሆን እንዲሁም ስራችን የት ድረስ እንደሚሄድና የስራ ኃላፊነታችን ምን ምን እንደሆነ በማስረዳት ላይ እንገኛለን ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ እኛ የውይይትን ስራ ማመቻቸትና ማሳለጥ እንጂ ወሳኞች ስላልሆንን ይህንን እያሳወቅናቸው ነውም ብለዋል።

አብላጫው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ብናገኝም አብረው ለመሥራት ፍላጎት ያላሳዩትም ኢትዮጵያ ሀገራቸው ነችና ያልሰሙንና ያልፈለጉን ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው ብለን እነሱን ወደ ኋላ መተው የለብንም።

ያልተቀበሉን ወይም የተቃወሙን የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደፊት ሁኔታዎች ከተመቻቹ ሀገር የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ስለሆኑ ህዝብ የተዋደደበትንና የተፋቀረበትን ጠንካራ ሀገርን መምራት ለፖለቲካ ፓርቲዎችም ትልቅ ዕድልና ጸጋ ይመስለኛልም ነው ያሉት።

ፕሮፌሰሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎችም ባሻገር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፤ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የአካል ጉዳተኛ ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም እዚህ ሀገር ያሉትን የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተወካይ አምባሳደሮችና አለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚመሩ ኃላፊዎችን ማግኘታቸውንም ገልጸዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን ከተቋቋመ ዘጠኝ ወራትን ያስቆጠረው ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቅቡልነቱ እየሰፋ መሆኑንና ወደፊትም ከዚህ በላይ ተቀባይነት እንደሚኖረው ያላቸውን ተስፋም ተናግረዋል።

# ከሰላም ስምምነቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሲቪክ ማህበራት ሁሉ የበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ዶክተር ንጉሱ ተናግረዋል።

የሰላም ስምምነቱ ያመጣውን ትሩፋት በመጠቀም ሀገር ለመገንባት በትብብር መስራት ይገባል ያሉት የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት፤ገንዘብ በማሰባሰብ የልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ፣ ሰብአዊ ድጋፎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሮች እንዲጎለብቱ ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የተጀመሩ ጥረቶችን ማገዝ አለባቸው ብለዋል።

ዶክተር ንጉሱ እንዳስታወቁት፤ ምክር ቤቱም ከሠላም ስምምነቱ በኋላ መንግሥት ያወጣቸውን ህጎች በተከተለ መንገድ መከናወን የሚገባቸው የድጋፍ ሥራዎች በተመለከተ በቀጣይ ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብሮችን በማውጣት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅታዊ ሥራ የበኩሉን ሚና ይወጣል።

የትግራይ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ተስፋዬ ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አመራሮችና አባላት ወደ ትግራይ በመምጣት በጋራ ለመስራት የሚያስችል ገንቢ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አቅማቸውን በማሰባሰብ ለሰብአዊ ድጋፍ፣ ለልማትና ለበጎ አላማ ማዋል ይችላሉ። አሁን ላይ የተፈጠረውን ሠላም በመጠቀም አሳታፊነት ባለው መልኩ ድጋፎችን በማቅረብ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

የትግራይ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት በሥሩ 72 ድርጅቶች አሉት፤ ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ጋር በመሆን ለሚከናወኑ የድጋፍ ሥራዎች በትብብር እንሰራለን። ተግባብተን ከሰራን የሕዝባችንን ችግር መቀነስ እንችላለን ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሔኖክ መለሰ በበኩላቸው፤ የሠላም ስምምነቱ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ዕድል ፈጥሯል። ይህን እድል ለመጠቀም የሚያስችል ውይይት በመካሄዱ በቀጣይ የሕዝቡን ችግር በሚያቃልሉ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በትብብር መንፈስ እንሰራለን ብለዋል።

አቶ ሔኖክ እንዳስታወቁት፤ ሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ሥራዎቻቸውን በቅንጅት ማከናወን ከቻሉ በጦርነት ወቅት የደረሱ ጉዳቶችን መጠገን የሚያስችል አቅም አላቸው። በተጨማሪም የሰላም ስምምነቱ ለሥራዎቻችን ውጤታማነት የበለጠ ጉልበት የሚፈጥር በመሆኑ ትብብርን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

ምክር ቤቱ በሀገሪቷ ዘላቂ ሠላምና ልማት እንዲጠናከርና ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ከአራት ሺህ በላይ የሀገር በቀል እና የውጭ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በማስተባበር እየሠራ ይገኛል።

# በደንበል ሐይቅ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፕሮጀክቱ ከውጭ የሚመጡ ቱሪስቶችን እና በአንድ ቀን በርካታ የህዝብ ቁጥር ማስተናገድ የሚችል ነው ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ፕሮጀክቱ አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን በሄክታር ደግሞ ከ30 ሄክታር በላይ የሀይቁን ዳርቻ የሚሸፍን ዘመናዊ የከተማ ፓርክ ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱን ወደ ተግባር ለማስገባት የአንድ ዓመት ዝግጅት ተደርጓል ያሉት የባቱ ከተማ ከንቲባ፤ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ገልጸው፤ ሥራው በቀጣይ ሳምንት ይጀመራል ብለዋል።

በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሼዶችን የመስራትና ለግንባታው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች የማውረድ ሥራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ፕሮጀክቱ ለሁለት ሺህ ያህል ወጣቶች የሥራ እድል እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

እንደ ከንቲባው ገለፃ፤ ፕሮጀክቱ በዘንድሮው በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ የታቀደው አንደኛ የሃራ ደንበል ሀይቅን ከብክለት ለመከላከል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የከተማውን የቱሪስት ፍሰት ለመጨመር ነው። ፕሮጀክቱ ከሥራ እድል ጋር ተያይዞ ለወጣቱ ዓሣና የተለያዩ እቃዎችን መሸጥ የሚችሉበት ሼዶች አሉት።

የደምበል ሃይቅ ዳርቻ ፕሮጀክት የአደባባይ በዓላትን ለማክበር እና ማንኛውንም ሃይማኖታዊና መንግስታዊ ትዕይንቶች ማስተናገድ የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ በብስክሌት አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ማስጓዝ የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ የሚሠራ ሲሆን፤ አብዛኛው የባቱ ከተማ ነዋሪም በብስክሌት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ፕሮጀክቱ ለከተማው ወሳኝ ነው ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ነዋሪዎች በሀይቁ ዳርቻ የእግር እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችሉበት እና ህፃናት የሚጫወቱበት የራሱ የሆነ ቦታ አለው ያሉት የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ፤ ፕሮጀክቱ የእግር ኳስ፣ የመረብ ኳስና ሌሎች መጫወቻዎች እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ ባለአንድ ፎቅ ካፌ ያለው ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱ የሃያ አራት ሰዓት የመብራት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ መሳሪያዎች የሚገጠምለት ነውም ሲሉ አክለዋል።

ፕሮጀክቱ የባቱ ከተማን በኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የቱሪዝም ገቢን ለመጨመር እና ከውጭ ሀገር ለሚመጡም ይሁን ለአካባቢው ነዋሪዎች ምቹ መኖሪያና የመዝናኛ ስፍራ እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

# በዞኑ 97 በመቶ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አቶ ፋንታሁን ቸኮል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014/2015 መኸር ከአጠቃላይ በዘር ከተሸፈነው 616 ሺህ 489 ሄክተር መሬት 97 በመቶ ሰብል ተሰብስቧል። ቀሪ ስራውም ውቂያ ብቻ ነው። በቁም ሰብል ግምገማ መሰረት በዞኑ 22 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት ይገኛል ተብሎም ይጠበቃል ብለዋል።

በኩታ-ገጠም ማሳ በስድስት ዋና ዋና የሰብል አይነቶች በጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ቦሎቄ እና የቢራ ገብስ ላይ በትኩረት ተሰርቷል። በእነዚህ ሰብሎች 368 ሺህ ሄክተር መሬት በክላስተር እርሻ ወይም በኩታ ገጠም የተሸፈነ ነው። በአካባቢው የጤፍ ክላስተር 195 ሺህ ሄክተር መሬት የሸፈነ ነበር። ከአጠቃላዩም 32 በመቶ ድርሻ አለው።

በተመሳሳይም በተያዘውም ዓመት ለስንዴ የተለየ ትኩረት በመስጠቱ 180 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የስንዴ ሰብል መልማቱን ጠቁመው፤ ከዚህ በፊት ከ140 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ አይበልጥም። ለአብነትም በዘንድሮው የምርት ዘመኑ በኮምባይነር ከተሰበሰበው የስንዴ ክላስተር በአማካይ 52 ኩንታል ምርት እየተገኘ ነው። በዚህም ዞኑ የ22 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት እቅዱን ያሳካል ሲሉ ተናግረዋል።

የጤፍ እና የስንዴ ክላስተር ማሳን ከማሳ ሳይሆን ቀበሌን ከቀበሌና ወረዳ ከወረዳ ያስተሳሰረ አሰራር ነው። በዚህም በባሶ ሊበን ወረዳ በአምስት ቀበሌዎች በአንድ ቀን ብቻ አስር ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል። ይህ ለቴክኖሎጂ በተለይም በኮምባይነር ምርትን የመሰብሰቡን ሂደት ውጤታማ የሚያደርግ በመሆኑ ጅምሩን ለማስፋት እየተሰራ ነው።

በዘመኑ አርሶ አደሩ ማሣውን የምርታማነት መጠናቸው ዝቅተኛ በሆኑ ሰብሎች እንዳይሸፍን ተደርጓል። የግብዓት እጥረት፣ የሰሜኑ ጦርነት እና ሌሎች ችግሮች ገበሬው ተረጋግቶ እንዳይሰራ ምክንያት ሆነው ነበር። ለምርት መጨመርና ለምርታማነቱ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ተገምቶ ነበር። ነገር ግን ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ ችግሩን መቅረፍ ተችሏል ነው ያሉት።

የማዳበሪያ እጥረት ለማቃለል ተፈጥሮአዊ ማዳበሪያን (ኮምፖስት) በሰፊው መጠቀም፣ በእጃችን እና እየቀረበ ያለውን ማዳበሪያ ቀድመው ለሚዘሩ ሰብሎችና ለሚዘሩ አካባቢዎች በቅደም ተከተል በፍትሀዊነት በማዳረስ ችግሩ ተፈትቷል።

የገበሬውን የገበያ ችግር ለመፍታት በተሰራው ሥራ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ውጤት በማምጣቱ የገበያ ችግር እየተፈታ ነው። ሃገራዊ የግብርና ውጤቶች የገበያ ሁኔታ መሻሻል፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ሸማቾች፣ የኮንትራት እርሻ ተግባራዊ መደረጉና ሌሎች ሰንሰለቶች አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን አስረድተዋል።

በዞኑ ከፍተኛ የስንዴ ምርት ቢኖርም በአካባቢው ገበያ ከሶስት ሺህ 800 እስከ አራት ሺህ ብር እየተሸጠ ነው። በዚህም አርሶ አደሩም ተጠቃሚና ደስተኛ እየሆነ ነው። የማምረት ችግር ካልሆነ በስተቀር የገበያ ችግር አለመኖሩንም አመላክተዋል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ‹‹ቪዚት ኢትዮጵያ›› መተግበሪያ የቱሪዝም ዘርፉ አዲስ መንገድ

ወርቅነሽ ደምሰው

ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ በመባል የሚታወቀው የቱሪዝም ዘርፍ በምጣኔ ሃብት ላቅ ያለ ውጤት ያስመዘገቡ ሀገሮች የጀርባ አጥንት እንደሆነ ይነገራል። ለቱሪዝም ዘርፍ ትኩረት ሰጥተው የሰሩ ሀገራት ከዘርፉ ከፍተኛ ገቢ እያገኙ ስለመሆናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ። በአንጻሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በቱሪዝም ሀብት የታደሉ ሀገራት ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ባለመሥራታቸው ማግኘት የሚገባቸው ሳያገኙ ቆይተዋል።

ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ለዘርፉ ተገቢ ትኩረት አለመሰጠቱን ተከትሎ ዘርፉ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የቱሪዝሙን ልማት ለማፋጠን የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ይሁንና አሁን የቱሪዝሙን የእድገት ማነቆ በማስወገድ የቱሪዝም ዘርፉን ለማዘመን የሚያስችሉ የዲጅታል መተግበራዎችን ለመጠቀም ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

በቅርቡ የቱሪዝም ሚኒስቴር ይፋ ያደረገው ዲጅታል የሞባይል መተግበሪያ ዘርፉን አንድ እርምጃ ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል መሆኑ ታምኖበታል። በዕለቱም የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ እንደተናገሩት፤ የቱሪዝም ሚኒስቴር ከተቋቋመ ጀምሮ ለዘርፉ ልማት እንቅፋት ሆኖ የቆየውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግር ለመፍታት የትኩረት አቅጣጫ አስቀምጦ በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል።

የቱሪዝም ዘርፉ ለማዘመን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የክፍያ ሥርዓቱን የሚያሳልጥ እና በጎብኚዎች ዘንድ መተማመንን የሚገነባ የቱሪስት ስማርት ካርድ ሥርዓት፣ የፕሮሞሽን ሥራዎችን በማቀላጠፍ የቱሪስት መረጃ ፍሰትን ቀላልና ምቹ በሆነ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የሞባይል መተግበሪያ ማበልጸግ መቻሉን ነው ሚኒስትሯ የገለጹት።

ይህ የቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ዘርፉን ለማዘመን ያበለጸገው ዲጅታል የሞባይል መተግበሪያ በውስጡ የዲጅታል ውጤቶች እና የጉዞ ማበረታቻዎች ያሉት መሆኑን ነው በቱሪዝም ሚኒስቴር የዲጅታል ቱሪዝም ፕሮሞሽን አማካሪ አቶ አማኑኤል አጋዤ የሚገልጹት።

እሳቸው እንደሚሉት፤ መተግበሪያውን በመጠቀም በአካባቢው ሊጎበኙ የሚችሉ የቱሪስት መስእቦች፣ በአቅራቢያቸው ያሉ ሆቴሎችን እና ባህላዊ ሬስቶራንቶችን እንዲሁም የመገበያያ ስፍራዎች በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። ጎብኚዎች የሆነ ቦታ /አካባቢ ላይ ቁጭ ብለው በአካባቢው የሚታዩ ነገሮች ሲፈልጉ በአካባቢው ሊጎበኙ የሚችሉ ቦታዎችን ያቀርብላቸዋል። አካባቢው ድረስ እንዴት መሄድ እንዳለባቸው፣ የሚሄዱበት ቦታ የአየር ንብረት ምን ይመስላል የሚለውን እና ስለቦታው አስቀድመው ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች ሙሉ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። የሞባይል መተግበሪያ ጎብኚዎቹ ቦታው ድረስ በጂፒኤስ ታግዘው እንዲሄዱ ጭምር የሚረዳ ነው።

"መተግበሪያው ለሀገር ውስጥ ጎብኚዎች በተጓዙ ቁጥር ነጥብ እየሰበሰቡ የሚሄድበትን አማራጭ የሚያቀርብ ነው" ያሉት አቶ አማኑኤል፤ አንድ ጎብኚ በጎበኛቸው ቦታዎች ብዛት ነጥብ እየሰበሰበ እንዲያከማች የሚያስችል ነው። ጎብኚው በሰበሰበው ነጥብ ልክ የሆቴል አገልግሎት፣ የመኪና እና የበረራ ቲኬት ቅናሽ ለማግኘት የሚያስችል እድል ይፈጥርለታል። ሌላው መተግበሪያ ለየት የሚያደርገው የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችል መሆኑ ነው። ቱሪስቶች ሲጎበኙ( ሲዝናኑ) የነበረውን ሁኔታ ወይም የጎበኙትን መስዕብ ፤ ፎቶ ተነስተው ወይም በአጫጭር ቪዲዮ መተግበሪውን በመጠቀም መለጠፍ ይችላሉ። እንደሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች እንደፌስ ቡክ፣ እንደ ዩቲዩብ እና ቲክቶክ በሚደረጉ መስተጋብሮች በለጠፉት ፎቶና ቪዲዮ ልክ መወደድ(ላይክ)፣ ማጋራት(ሼር) እና ሀሳብና አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ የሚያስችል ነው። ከዚህ በሻገርም ባገኙት ብዙ

**መተግበሪያው ከሚኒስቴሩ አንጻር የቱሪስት መረጃ(ዳታ) በመሰብሰብ የሚረዳ ሲሆን፣ ምን ያህል ጎብኚዎች አንድን መስህብ እንደጎበኙትና የቆይታ ጊዜያቸው ስምን ያህል ጊዜ እንደነበር እና ሌሎች መረጃዎችንም ይሰጣል፡፡ ሌላው ማዕከላዊ የሆነ አስተዳደር እንዲኖር በማድረግ በጎብኝቱ ሂደት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመሰብሰብ ውሳኔ ስመስጠት የሚረዳ ግብዓት ስመስጠትም ይጠቅማል**

የመወደድ፣ የማጋራት እና ሀሳብና አስተያየት መጠን ማበረታቻ የሚያገኙበት ሥርዓት የተዘረጋለት ነው። ለእነዚህ ጎብኚዎች ተፅዕኖ መፍጠር የቻሉ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ላይ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያተረፉ በማለት ሚኒስቴሩ ማበረታቻ የሚሰጥ እንደሆነ ነው አቶ አማኑኤል የሚያስረዱት።

አንድ ጎብኚ ነጥብ ለመሰብሰብ ብዙ አማራጮች አሉት። የጎበኛቸውን ቦታዎች መወደድንና አጭር ማስታወሻ መጻፍ ነጥብ ያስገኛል። ለምሳሌ ባሌ ብሔራዊ ፓርክ ወደደኩት የሚል እዚያ ላይ አስተያየት ከጻፈ ነጥብ ያገኛል። ሌሎች የለጠፉትን ወይም ያጋሩት ምስል ወይም ቪዲዮ ከወደደ ነጥብ ያገኛል። አንድ ጎብኚ ቢፈልግ ፎቶ ወይም ቪዲዮ ሲለጥፍ ወይም ሲያጋራ ነጥብ ይሰበሰባል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ጎብኚ መጀመሪያ ሲመዘገብ እንኳን ደህና መጣህ ለማለት የማበረታቻ ነጥብ እንደሚሰጠው ያብራራሉ።

ጎብኚ ያልሆኑ ሰዎች የሚያገኙት ነጥብ ትንሽ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ አማኑኤል ፤ ምክንያቱም ጎብኚ ካልሆኑ የሚያገኙት ነጥብ የተለጠፈውን መወደድን የሚገልጽ እንጂ ልምዱን ለማካፈል የሚያስችል አለመሆኑን ይናገራሉ። የነጥብ ማበረታቻ መስጠት ዓላማው ሌሎች ጎብኚዎች ለማበረታት የሚጠቅም ነው። ሰዎች የጎበኙትን ቦታ ሲለጥፉ ሌሎች ላይ መነሳሳትን በመፍጠር እንዲጎበኙት እንደሚያደርግ ነው የሚናገሩት። ‹‹ለአብነት እኔ ወንጪ በመጎብኘት ፈረስ ላይ ሆኜ የተነሳሁት ፎቶ ብለጥፍ ሌሎች አይተው እዚህ ቦታ መሄድ አለብኝ ብለው ማነቃቃትና መነሳሳትን እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል›› ይላሉ።

የሞባይል መተግበሪያ ለቱሪዝም ያለውን ጠቀሜታ ከቱሪስቱና ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አንጻር ነጣጥሎ ማየት እንደሚቻል የሚገልጹት አቶ አማኑኤል፤ ከቱሪስቱ አንጻር ሲታይ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት የት መሄድ፣ ምን መጎብኘት ፣ እንዴት መሄድ እንዳለባቸው፣ በአካባቢያቸው ያለውን የሆቴልም ሆነ ማረፊያ ቦታ፣ ሬስቶራንት እና የመሳሰሉትን መረጃዎች በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ ደግሞ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንዲበረታቱ ያደርጋል፤ አገልግሎቶችን በቅናሽ እንዲያገኙ በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉ እንዲነቃቃ ያደርጋል ብለዋል።

ከሚኒስቴሩ አንጻር የቱሪስት መረጃ(ዳታ) በመሰብሰብ የሚረዳ ሲሆን ምን ያህል ጎብኚዎች አንድን መስእብ እንደጎበኙትና የቆይታቸው ጊዜያቸው ለምን ያህል ጊዜ እንደነበር እና ሌሎችን መረጃ የሚሰጥ ነው። ሌላው ማዕከላዊ የሆነ አስተዳደር እንዲኖር በማድረግ በጎብኝቱ ሂደት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመሰብሰብ ውሳኔ ለመስጠት የሚረዳ ግብዓት ለመስጠት እንደሚጠቅም ነው አቶ አማኑኤል የሚገልጹት። ሚኒስቴሩ እዚሁ ሆኖ ሁሉንም መቆጣጠር የሚቻልበት ሁኔታ የተመቻቸ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የቱሪስት መስዕቦች በተቻለ መጠን ለማስተዋወቅ እንደሚጠቅም አስረድተዋል።

ሞባይል መተግበሪያ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ብዙ ሰዎች ተቀብለውት ወደ ተግባር ተገብቷል ያሉት አቶ አማኑኤል፤ ይፋ ከተደረገ በሁለት ቀናት ውስጥ አምስት መቶ በላይ ሰዎች አውርደው ጥቅም ላይ እንዲውል እንዳደረጉት ይገልጻሉ። የእግር ጉዞ አዘጋጆች፣ እየተጠቀሙበት እና የማስተዋወቅ ሥራ እየሰሩበት እንደሆነ ጠቁመው፤ እንደመጀመሪያ ከተጠበቀው በላይ ውጤት ማሳየቱን ተናግረዋል። በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረትም ከዚህ በላይ እንዲሻሻል የሚፈለጉ ብዙ ነገሮች ስላሉ እነዚህ ተሻሽለው ማስታወቂያ ከተሰራለት ደግሞ ከዚህ የበለጠ የቱሪዝሙን ማህበረሰብ የመጠቀም ባህልን ከፍ ያደርጋል ይላሉ።

በቀድሞ የቱሪዝም ድርጅት ከዚህ በፊት የበለጸገ ሞባይል መተግበሪያ ምድረ ቀደምት /ላንድ ኦፍ ኦሪጅን/ የሚባል እንደነበር ያስታወሱት አቶ አማኑኤል፤ ይህ የሞባይል መተግበሪያ በሚጫንበት ጊዜ ልክ እንደ ድረገጽ መረጃዎች ብቻ የሚሰጥ እንደሆነ ይናገራሉ። ለምሳሌ ባሌ ተራሮች፣ ላሊበላ እና የመሳሳሉት የቱሪዝም መስዕቦችን በመጠቅስ ስለመስዕቦቹ የሚያብራራ ነው። ከአርተፊሻል ኢንተለጀንሲና ከጂፒኤስ ጋር የተገናኘ ምንም አይነት አገልግሎት የሚሰጥ ባለመሆኑ ኋላቀር እንደነበር ያብራራሉ።

በግሉ ሴክተር የበለጸጉ ሞባይል መተግበሪያዎችም ቢኖሩም ውስን ቦታዎች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን ነው የሚገልጹት። ለአብነት በሆቴል፣ በመኪና እና በመሳሰሉት ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉ እንደሆኑ አንስተው፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ መረጃን ለማግኘትና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ መተግበሪያዎች በጣት የሚቆጠሩ እንደሆነ አመላክተዋል።

መተግበሪያ እውን እንዲሆን ለማስተዋወቅ ከተለያዩ የማስተዋወቂያ ድርጅቶች ጋር ውል መፈረሙን የሚናገሩት አቶ አማኑኤል፤ የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲያስተዋውቁ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ውጭ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ድረገጾችን በመጠቀም ዲጅታል መተግበሪያዎች ለማስተዋወቅ ፕሮግራም መያዙን ጠቅሰው፤ አሁን ላይ የመተግበሪያውን አጠቃቀሙን የሚሳዩ አጫጭር ቪዲዮዎችን እየተሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል። ቪዲዮዎቹ አልቀው ህብረተሰቡ ዘንድ ሲደርስ ብዙዎች እንደሚጠቀሙት ነው ያብራሩት።

የሞባይል መተግበሪያው የሚጠቀሙት የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ሲሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች መተግበሪያውን ተደራሽ በማድረግ እንዲጠቀሙ ለማስቻል ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ሞባይል መተግበሪያ ጋር የማስተሳሰር የሚቻልበት ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ እንደሆነ ነው የሚገልጹት። በተጨማሪም ባነሮች በምታዩበት ቦታዎች ላይ በመስቀል፣ ቪዲዮዎች መሥራት አውሮፕላን ውስጥ በመልቀቅ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከአየር መንገድ ጋር በመነጋገር እየተሰራ መሆኑ ተናግረዋል።

የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ፕሌይ ስቶር ላይ ገብተው ‹‹ቪዚት ኢትዮጵያ›› የሚለውን የሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም አውርደው በመጫን መጠቀም ይችላሉ። አስተያየት ካላቸው በማስፈር በሚጓዙበት ሁሉን ያዩት፣ የመሰጣቸውን ነገሮች ቪዲዮና ፎቶ እያነሱ በማጋራት ነጥብ ይሰብሰቡ። በሰበሰቡት ነጥብ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሁም መግቢያዎች ላላቸው መስዕብ የተቀመጡ ማበረታቻውን ቅናሾችን እና ነጻ ማግኘት የሚቻሉበት ሁኔዎች ተመቻችተዋል። በተጨማሪም ነጥብ አሰጣጡ እስከ አምስት ደረጃ ያለውን ስለሆነ ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ እውቅና የሚያሰጥ በመሆኑ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ እውቅና ለማግኘት ይጠቀሙ ሲሉ አቶ አማኑኤል መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ።

ኢንጂነር መላኩ ሙካ በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የሳተላይት ኦፐሬሽን ዳይሬክተር ናቸው። ‹‹ቪዚት ኢትዮጵያ›› የተሰኘውን የመተግበሪያውን ቴክኒክም የሚመሩት እርሳቸው ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የሞባይል መተግበሪያ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ነው። አንደኛው ጎብኚዎች የተለያዩ መዳረሻዎችን በጂፒኤስ በመጠቀም እንዲያስሱ የሚያደርግ ሲሆን ማንኛውም ጎብኚ መዳረሻዎች ወዳሉበት እንዲሄድና በአካባቢው ያሉ የሆቴል፣ ሬስቶራንት እና የመሳሰሉት የተለያዩ አገልግሎቶችን ቦታው ድረስ መሄድ ሳያስፈልገው ባለበት ቦታ ሆኖ እንዲያወቅ የሚረዳ ነው። በተጨማሪም ለጉብኝት የሚሄድበት መዳረሻ የአየር ፀባይ ሳይቀር አስቀድሞ መረጃ እንዲያገኝ ያስችላል።

ሁለተኛው ጎብኚዎች ለጉብኝት የተለያዩ አካባቢ በሚሄዱበት ጊዜ ያገኙትን የጎብኝት ልምዶችን የሚያጋሩበት ነው። እንደ ፌስቡክ እና ኢንስተግራም ላይ እንደምናየው መረጃዎች የተለያዩ የቱሪስት መስእቦችን በማስተዋወቅ ብዙ ሰዎች እንዲጋሩት ለማድረግ የሚያገለግል ነው።

ሦስተኛው ጎብኚዎች መተግበሪያውን በመጠቀም የቱሪስት መዳረሻዎች እንዲሁ ባህሎች በሚያስተዋወቅበት እና ለሌሎች በሚያጋሩበት ጊዜ በሚሰበስቡት ነጥብ ማበረታቻ የሚያገኙበት ሥርዓት የተዘረጋለት ነው። አራተኛውና የመጨረሻው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክብረ በዓላትንና ፌስቲቫሎችና ብሔራዊ በዓላት ለማወቅ(ማግኘት) የሚያስችል ነው።

ከሞባይል መተግበሪያው በተጨማሪ ሚኒስቴር የሚቆጣጠርበት አድሚንስትሪሽን ዳሽ ቦርድ ተሰርቷል ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህንን አድሚንስትሪሽን ዳሽ ቦርድ ተጠቀመው ወደ ሞባይል ሲስተሙ ማስገባት የሚፈልጉት ዳታዎች፣ ስታስቲኮችን እና ሪፖርቶችን እንዲሁም ግብረ መልሶችንም የሚያስገቡት እንደሆነ አመላክተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የሞባይል መተግበሪያ አብዛኛው የቱሪዝም መረጃዎችን እንዲያጠቃልል ተደርጎ የተሰራ ነው። እስከዛሬ ከተሰሩት ሰፊ የሆኑ ሥራዎችን ያካተተ ነው። ሁሉን ነገር በአንድ የያዘ ወደፊትም የተለያዩ ነገሮች እየተጨመሩበት እየሰፋ እና እየደገ የሚሄድ ነው። የቱሪዝም ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ መደገፍ የሚያስችል አንዱ ወጥ የሆነ በቱሪዝም ዘርፍ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ አሟልቶ የያዘ ነው።

መተግበሪያ ይፋ ከተደረገ በኋላ የሰዎችን አመላካከትን እንደቀየር የሚገልጹት አቶ መላኩ፤ ቱሪዝም ለአንድ አካል ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን ሁሉም ዜጋ ሀገሩን ማስተዋወቅ አካባቢ ያሉት የተለየ የቱሩዝም መስዕቦች የማወጣት ሥራዎች የመሥራት ግዴታውን መወጣት እንዳለበትም ያመላከተ ነው ይላሉ። መተግበሪያውን በመጠቀም የተለያዩ ሰዎች አካባቢያቸው ያሉ መስእቦችን በማስተዋወቅ በማጋራት ሌሎች እንዲያውቋቸውን በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስተጋብሮች እንዲኖር ማስቻሉ ያስረዳሉ።

ከዚህ ቀደም የበለጸጉት መተግበሪያዎች የውጭ ጎብኚዎች ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉ ነበሩ ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህም በኮቪድ ወቅት ሀገሪቱ በእጅጉ የጎዳ በመሆኑ ለሀገር ውስጥ ትኩረት በመስጠት ቱሩዝምን እንዲበረታታ ምክንያት መሆኑን ይገልጻሉ። ይህ መተግበሪያ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ስለሀገራቸው በቂ መረጃ ኖራቸው እንዲሰሩ የሚያበረታታ ስለሆነ ማንኛውም ሰው መተግበሪያው ከአፕ ስቶር እና ከፕሌ ስቶር አውርዶ መጠቀም ይችላል ብለዋል።

በተለይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች መተግበሪያውን በመጠቀም የሀገራቸውን የቱሪዝም መስዕቦች እንዲያስተዋወቁ ማድረግ ይጠበቃል። የጎበኙትን የተለያዩ መስእቦችን በማጋራትና በማስተዋወቅ ሀገራቸውን እንዲያውቁ በማድረግ አጋዥ በመሆን ሀገራቸውን መጠቅም እንዳለባቸው ነው አቶ መላኩ ለዝግጅት ክፍላችን ያሳወቁት።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የንብረት ታክስ አንድምታ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



አቶ ታምራት አስሙ



አቶ በፍርዴ ጥላሁን

የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ባካሄዱት የጋራ ልዩ ስብሰባ በንብረት ላይ የሚጣል ታክስ ስልጣን ለክልሎች እንዲሰጥ ተወስኗል። በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በንብረት ላይ የሚጣል ታክስ ስልጣን ለክልሎች የሚሰጥ ሆኖ ክልሎች ደግሞ ባላቸው ህገ-መንግስታዊ ስልጣን ለአካባቢ መስተዳድሮች እንዲሰጡ የሚል ነው።

የንብረት ታክስ በከተሞች እና በክልሎች ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን፣ ሌብነትን ለመከላከል፣ የታክስ አማራጮችን ለማስፋት፣ ክልሎች ከድጎማ ተላቅቀው የመልማት እድላቸው እንዲሰፋ፣ ለከተሞች የመሰረተ-ልማት አቅርቦትና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማጠናከር እና በከተሞች የስራ አጥነት ችግር እንዲቀረፍ የሚያግዝ የውሳኔ ሀሳብ ስለመሆኑ በስፋት ተብራርቷል።

ለመሆኑ የንብረት ታክስ በኢትዮጵያ ሲተገበር አንድምታ ምንድን ነው፤ ምን ጥቅም፣ ምንስ ስጋት አለ፤ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ምን ይመስላል በሚለው ዙሪያ መረጃዎችን አገላብጠን ባለሙያዎች አነጋግረን የሚከተለውን ትንታኔ አዘጋጅተናል።

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የንብረት ግብር (ፕሮፐርቲ ታክስ) ማለት፤ አንድ ግለሰብ አሊያም ሕጋዊ አካል ለሚጠቀምበት ንብረት ለመንግሥት የሚከፍለው ገንዘብ ማለት ነው። በአብዛኛዎቹ የዓለም አገራት የንብረት ግብር የሚለካው ንብረቱ በየዓመቱ ተተምኖ የሚኖረውን ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው። በርካታ የዓለማችን ከተሞች የንብረት ግብር ጥለው በሚሰበስቡት ገንዘብ ራሳቸውን ይደጉማሉ። አብዛኛውን ጊዜ የንብረት ግብር የሚጣልበት መሬት እና ሕንፃ ቢሆንም ተሽከርካሪዎች ላይም ግብር የሚጥሉ አገራት አሉ።

የንብረት ግብር አሜሪካ ውስጥ የማዕከላዊው መንግሥት እና ክልላዊ አስተዳደሮች ከሚሰበስቡት ገቢ 30 በመቶውን ይይዛል። ነገር ግን አሜሪካ ዝቅተኛ የንብረት ግብር ከሚያስከፍሉ አገራት መካከል ስትሆን፣ ቤልጂዬም እና ስፔንን የመሳሰሉ አገራት ደግሞ ከፍተኛው የንብረት ግብር በማስከፈል የሚታወቁ አገራት ናቸው።

የባንክ ባለሙያው አቶ ታምራት ዓለሙ እንደሚሉት፤ የንብረት ግብር (ፕሮፐርቲ ታክስ) ማለት፤ አንድ ግለሰብ አሊያም ሕጋዊ አካል ለሚጠቀምበት ንብረት ለመንግሥት የሚከፍለው ገንዘብ ነው። የንብረት ታክስ ዘርፈ ብዙ ትንታኔዎችን የሚጠይቅ ስለመሆኑም ይናገራሉ። ፕሮፐርቲ ታክስ ሥርዓት ከአገራት የገቢ ማግኛ ስልቶች ውስጥ ቀዳሚው ሲሆን ሥርዓቱ በአግባቡ አንዴ ከተዘረጋ ገንዘቡን ለመሰብሰብም ብዙ አስቸጋሪ የማይሆን ስለመሆኑም ያብራራሉ። የዚህ ግብር በባህሪው ለመሰወር የማይመችና በብዛት መሬት ወይንም ቤት ነክ በሆኑ ንብረቶች ላይ የሚጣል ግብር ነው። ይህም ደግሞ የኢኮኖሚ ትልቁ ምንጭ በመሆኑ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ያብራራሉ። እንዲሁም የቴክሎጂና የሳይንስ ዕድገት መገለጫ ጭምር ነው።

የንብረት ታክስ ሲሰበሰብ ከሞላ ጎደል ሥርዓቱ የፋይናንስ ህግን ተከትሎ የሚሰራ እና ገንዘብ ዝውውሩንም ወደ ባንክ ሥርዓት የሚያመጣው ስለሚሆን የፋይናንስ ተቋማትን አቅም ለማጎልበትም የራሱ የሆነ ፋይዳ አለው። ገንዘብ ወደ ባንክ ስርዓት ከመጣ ደግሞ መንግስትና ህዝብ የሚጠቀሙበት ዕድል ሰፊ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ዜጎች ቁጠባን እንዲለማመዱ አሊያም ደግሞ ብክነትን ለማስቀረት ያግዛቸዋል የሚል እምነት አላቸው። በአንድ አገር ውስጥ የገቢ ዕድገት ማምጣት ማለት የህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የመመለስ አቅምን ከማሳደጉም በላይ በአንድ አገር ጠቅላላ ምርት ዕድገት እና በአገር ጠለላ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይም የራሱ አወንታዊ ሚና ይኖረዋል።

እንደ አቶ ታምራት ማብራሪያ ከሆነ፤ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን እየፈለጉ ገንዘብ መሰብሰብ የሚበረታታ ቢሆንም በጥቅሙ ልክ ጉዳትም እንዳለው ግን ማጤን ይገባል ይላሉ። መንግስት ብር ከዜጎች በብዛት በሰበሰበ ቁጥር ለብዙ ነገር ስለሚያውለው በተቃራኒው የገንዘብ መጋሸብን የማስከተል ዕድል ይኖረዋል። ታክሱ በበዛ ቁጥር ሰዎች ቤት የመግዛት ዕድል ሊቀንስ እና በዚያው ልክ የገንዘብ ፍሰትን ሊገድብ ስለሚችል ይህም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል። የመንግስት ገቢ ቢጨምርም የሚመጣው ገቢ በምን ሁኔታ መቆጣጠር ይገባል የሚለው ደግሞ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ያሳስባሉ።

የንብረት ታክስ አዋጭ እና ስኬታማ ሊሆን የሚችለው የኢኮኖሚውን ምህዋር ሊዘውሩ የሚችሉ ሥርዓቶችን መቆጣጠር ከተቻለና እና የሚመጣው ገንዘብ በምን አግባብ ወደ ኢኮኖሚው መግባት አለበት የሚል ሳይንሳዊ ስሌትን ሲከተል ነው። ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን የንብረት ታክስ ጉዳት ሊኖረው ይችላል የሚል ሙያዊ አስተያየት አላቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ማመን ከሚቻለው በላይ ቤቶች በውድ ዋጋ ተገንብተው በውድ እየተሸጡ ነው። ዳያስፖራውን ጨምሮም በርካቶች ንብረታቸውን ወደማይንቀሳቀስ ንብረት እየቀየሩ ነው። ይህ በራሱ የሚያመላክተው መንግስት በንብረት ላይ የሚጥለው ታክስ የተወሰነ መሆኑን ነው። ይሁንና በእነዚህና መሰል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ የንብረት ግብር መጣሉ የሚበረታታ ቢሆንም በጣም የተጋነነ የንብረት ግብር የሚጣል ከሆነ ግን የሪል እስቴት ወይንም የቤት ግንባታ ስርዓትን እንዳያቃውሰው መጠንቀቅ እንደሚገባም ያብራራሉ።

በሌላ ጎኑ ደግሞ መንግስት በንብረት ላይ የሚጥለውን ታክስ ለማካካስ ሲባል፤ የህንፃ ባለቤቶች ወይንም የቤት ባለንብረቶች በተከራዮች ላይ ዋጋ የሚጨምሩ ይሆናል። ይሄ ሲሆን በኑሮ ውድነቱ ላይ ሌላ እክል የሚፈጥር በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የማስከተል ዕድል እንዳለውም ይጠቁማሉ። ይህ ደግሞ የቢዝነስ እንቅስቃሴዎችን እስከመገደብ አቅም ያለው እንደሆነም ያስረዳሉ። በመሆኑም የንብረት ግብር ሂደቱና ውጤቱ በድምር ውጤት አገራዊ ትርጉም ያለው በመሆኑም ጥንቃቄ የተሞላው አሰራር መዘርጋት እንዳለበት ይጠቁማሉ።

የህግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ምንም እንኳን በጠንካራ ህግና አሰራር ላይ የተመሰረተ ባይሆንም፤ የንብረት ግብር ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት መሆኑን ያስታውሳሉ። በዘመነ ደርግ ደግሞ ይህ ሥርዓት በተወሰነ ደረጃ መልኩን ቀይሮ የመሬት እና የጣሪያ ግብር ዜጎች እንዲከፍሉ ማድረግ የተጀመረ ቢሆንም በገቢ ደረጃ ግን አጥጋቢ የሚባል አለመሆኑንም ይናገራሉ። በዘመነ ኢህአዴግም እንደ ሁኔታው የግብር ክፍያ በሚል ክፍያዎች ይከናወኑ እንጂ መንግስትን በመጥቀም ደረጃ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ሆኖም በአሁኑ ወቅት የንብረት ታክስ ጉዳይን በአዲስ መንገድ ለማየት መመከሩ ክፋት የለውም ባይ ናቸው።

የንብረት ታክስ ሲባል ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እሳቤዎችን ያዘለ መሆኑን የሚጠቁሙት አቶ በፍርዴ፤ ይህ ሥርዓት የንብረት ግብር በኢትዮጵያ ሁኔታ የጣሪያ እና ግድግዳ ግብር በሚል ቀደም ሲል በወጣ አዋጅ እስካሁን ድረስ የሚከፈልበት አግባብ የነበረ ሲሆን መንግስት የሚያገኘው ጥቅም እጅግ አነስተኛ የሆነበት አሰራር ነው።

በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሰዎች የጣሪያ እና ግርግዳ በሚል ከሚከፍሉት እጅግ ዝቅተኛ ገንዘብ ውጭ ንብረቱ የራሳቸው በመሆኑና በዚያው ልክ በሚያገኙት ጥቅም ግብር አለመክፈላቸው አግባብ እንዳልነበር ይጠቁማሉ። በዘመነ ኢህአዴግም ይህ ህግ ጠንካራ መሠረት ኖሮት አገር እና ህዝብ የሚጠቀምበት ሥርዓት ሳይዘረጋ መቆየቱን ያስታውሳሉ። ታዲያ ይህ በመቅረቱ አገር ማግኘት ከነበረባት ጥቅም ብዙ ቢሊዮን ብሮችን ማጣቷን ይጠቁማሉ። የንብረት የግብር ዓይነት በአሁኑ ወቅት አንዱ የገቢ ማግኘት ስልት ተደርጎ መወሰዱና በአሁኑ ወደ ትግበራ የሚያስገቡ ምዕራፎችን ለመዳሰስ መሞከሩ የሚበረታታ ነው፤ እንዲያውም እጅግ በጣም የዘገየ ጉዳይ ስለመሆኑም ያብራራሉ።

አቶ በፍርዴ እንደሚሉት፤ በየትኛው ዓለም መንግስታት ገቢያቸውን የሚሳድጉበትን አማራጭ በሰፊው ይመለከታሉ። ይሁንና በምን ሁኔታ እና አግባብ እንጠቀም የሚለው ግን ፈተና ሊሆንባቸው ይችላል። በዚህ አግባብም የኢትዮጵያ መንግስት የንብረት ታክስን ተግባር ላይ ለማዋል ማሰቡ የሚበረታታ መሆኑን በመጠቆም ምን ዓይነት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ የሚለውን ግን በጥልቀት ማሰብ እንደሚገባ ያሳስባሉ።

የንብረት ግብር በብዛት የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ያካተተ ቢሆንም በብዛት ውጤታማ የሚሆነው ግን በማይንቀሳቀሱት ላይ ስለመሆኑም ይጠቁማሉ።

በርካታ ሰዎች በስማቸውም ይሁን ካለስማቸው ከፍተኛ ሃብት ያጋበሱ ሲሆን፤ ይህ የንብረት ታክስ ግን በአግባቡ ከተሰራበት ለዚህም መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ይሆናል። ከዚህም በዘለለ ንብረቱ የማነው ብሎ በትክክል ለመለየትና ለመቆጣጠርም ጭምር ያግዛል። ይህ አካሄድ ደግሞ በአንድ አገር ውስጥ ሊፈፀም የሚችልን የንብረት ስወራ እና ሙስናንን በማስቀረት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። የንብረት ታክስ መንግስት ገቢ ከሚያገኝባቸው በርካታ አማራጮች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ መሰረት ልማቶችን ለማስፋፋት፣ ከህዝቡ የሚነሱ የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ ጠንካራ የፋይናንስ መሰረት እንዲኖረውም የሚያደርግ መሆኑን ያብራራሉ።

የባንክ ባለሙያው አቶ ታምራትም ሆኑ የህግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት መደረግ አለበት ሲሉ ይናገራሉ። የንብረት ታክስ ህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ አካላት የሚጠቅም ወይንም የሚጎዳ ነው ብሎ ከወዲሁ ከመበይን ይልቅ ከሁሉም በፊት የታክሱ መጠንና የስሌት አውዱ መታወቅ አለበት። በሌላ ጎኑ ደግሞ ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ይህ የግብር አጣጣልና ብያኔ የተለመደ እና በርካታ አገራትም እየተጠቀሙበት ስለመሆኑም ማወቅ ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ነው።

ይህም በመሆኑ መንግስት ከአፍሪካ ብሎም ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመቅሰም ወደ ተግባር መቀየር አለበት። ይሁንና በትግበራ ወቅት ፈተናዎች ሊያገጥሙ ስለሚችሉም የመውጫ መንገዶችን ከወዲሁ ማሰብ እንደሚገባም ይጠቁማሉ። የተጋነነ የንብረት ታክስ ሆነ ከመጠን የወረደ የንብረት ታክስ አጣጣልም እንዳይከሰት ከወዲሁ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል የሚል ሙያዊ ምክረ ሀሳብ አላቸው።

**የንብረት ግብር (ፕሮፐርቲ ታክስ) አንድ ግለሰብ አሊያም ሕጋዊ አካል ለሚጠቀምበት ንብረት ለመንግሥት የሚከፍለው ገንዘብ ማለት ነው። በአብዛኛዎቹ የዓለም አገራት የንብረት ግብር የሚለካው ንብረቱ በየዓመቱ ተተምኖ የሚኖረውን ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው። በርካታ የዓለማችን ከተሞች የንብረት ግብር ጥለው በሚሰበስቡት ገንዘብ ራሳቸውን ይደጉማሉ**

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ሴት ታራሚዎችና የህይወት ገጽታቸው

**ሰላማዊት ውቤ**

ቃሊቲ በሚገኘው በፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ማዕከል ተገኝተናል። ዕለቱ የጥምቀት በዓል ዋዜማ ከተራ ነበርና ሴት ታራሚዎች ለበዓሉ ዝግጅት ሽር ጉድ እያሉ ነው ። ደማቅ ቀይና አዲስ አልባሳት የለበሱት ሴት ታራሚዎች የሚንቀሳቀሱበትና የሚኖሩበት ሥፍራ ፅአዳነት በአግራሞት ያስደምማል። ተደራራቢው አልጋቸው የዩኒቨርሲቲን መኝታ ክፍል ያስታውሳል። እዛም እዚህም የተፈጨ ሽንኩርት ይበስላል። በማዕከሉ እየተጋገረ ያለው የትኩስ እንጀራ ሽታ ለአፍንጫ ጡዑም ማዕዛ ከመለገስ አልፎ የሰውን ልብ እጅግ አድርጎ ያስደስታል። ለበዓሉ ዋዜማ ከተራ የተሰራውም ገበታ ግርማ ሞገስ ያለው ነበር። በማግስቱ በታላቅ ድምቀት የሚከበረው የጥምቀት በዓል ዕለት ደግሞ ታላቅ የምሳ ግብዣ አላቸው። የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓልም በዚሁ መልኩ ማሳለፋቸውንም ነው የሚናገሩት።

ሁሉም ያነጋገርናቸው ሴት ታራሚዎች በማረሚያ ቤቱ በዕለቱ ታቦታት ይወጣሉ። በዓሉም በድምቀት ይከበራል። በሳቅ በጨዋታ በምግብ መጠጥ፤ ታራሚዎች ቤተሰባቸውን እንዳያስታውሱና ደስተኛ ሆነው እንዲውሉ ይደረጋል። ለአውድ ዓመት ብቻ ሳይሆን ለሰርክ ቀናትም በማረሚያ ቤቱ የሃይማኖት መቻቻል አለ። በየማረፊያቸው ሁሉም ዓይነት ዕምነት ተከታዮች በየዕምነታቸው ፀሎት ያደርጋሉ። በተለይ ለበዓላት በሚደረገው ዝግጅት ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር በሥራም ሆነ በመዋጮ እኩል ይሳተፋል። እዚህ ጋር በማረሚያ ቤቱ ማረፊያ ቤት የሚገኙ ታራሚዎች ተሳትፎም እጅግ የጎላ ነው። እነሱ ለኢትዮጵያዊያኑ በዓል ኢትዮጵያዊያኑ ደግሞ ለውጭ ዜጎቹ በዓላት (ኪሪስማስ) ከመሥራት ጀምሮ ይረዳዳሉ። ማረሚያ ቤቱ ለበዓል ዝግጅት ከወትሮው ለየት ያለ በጀት ይመድባል። በዚህ ላይ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤቱ ሠራተኞች ጋር በመቀናጀት ከውጭ ለበዓል መዋያ ድጋፍ ያመጣሉ። አንዳንዶቹም ማረሚያ ቤቱ በሰጣቸው ስልጠና የተለያዩ የእጅ ሙያ ባለቤቶች በመሆናቸው የሰሩትን ለገበያ አቅርበው ከሚያገኙት ገቢ ወይም ከሚያመርቱት ምርት ለበዓል ይቆጥባሉ፤ ያዋጣሉ፤ ስጦታ ይሰጣጣሉ።

በአጠቃላይ እኛ በጥምቀት ዋዜማ አግኝተን ያነጋገርናቸው ታራሚዎች ደስታ የፈነቀለው እንቅስቃሴያቸው በፍፁም ወደ ማዕከሉ ለእርምት የገቡ አላስመሰላቸውም። ዝግጅቱ ማዕከሉ ራሱ ሴቶች ከጥፋታቸው የሚታረሙበት የቅጣት ቦታ መሆኑን የሚያስረሳ ነው። እንዲህ ባለው ዐውድ ዓመት ወቅትና መልካም አያያዝ ወደ ማረሚያና ማረፊያ ማዕከሉ መግባቷን የምታስታውሰው የ20 ዓመት ፍርደኛ የሕግ ታራሚ አስናቀች ጌታቸው በገባችበት ወቅት መልካም አያያዙና ዝግጅቱ ለጥፋት ቅጣት የሚሰጥበት ማረሚያ ቤት መግባቷን ያስረሳት መሆኑን ታወሳለች። "ጓዜን ይዤ ከገባሁ በኋላ ለሰዓታት ቁጭ ብዬም በቅጣት ወደ ማሳልፍበት አስፈሪ ቦታ እስኪወስዱኝ ስጠብቅ ቆይቻለሁ" ስትልም ታስታውሳለች። አስናቀች ወደ እስር ቤት እስክትወሰድ የምትቆይበት ማረፊያ በመሰላት ቦታ ነፃነታቸውን እየተመኘችና እያደነቀች ቆይታለች። ከሰዓታት ቆይታ በኋላ ከሰል እያቀጣጠሉ ሁሉ ምግብ ያበስሉና በነፃነት ከወዲያ ወዲህ ሽር ጉድ ይሉ የነበሩት ሴት ታራሚዎች እየመጡ አመጣጧን ከጠየቋት በኋላ ቦታው ታስራ መቆያዋ እንደሆነ የነገሯት መሆኑንም ደስታ በፈነቀለው ፈገግታ ትናገራለች። "ዕውነት ጥፋት አጥፍቼ ነው ወይ የገባሁት?" ብላ ባለማመን ራሷን መጠየቋንም ትገልፃለች። ጥፋት ቢያጠፉ በህግና ደንቡ መሰረት የሚቀጧቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያሳይዋቸው ትህትና እና ትዕግስት፤ የሚያደርጉላቸው እንክብካቤ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። በታራሚዎች ላይ የሚፈጸም የሙብት ጥሰት አለመኖሩንም አፏን ሞልታ ታነሳለች። ይልቁንም ሴት ታራሚዎች የበለጠ ሰርተው በነፃነት እንዲኖሩ በማረሚያ ቤቱ አመራሮች ይበረታታሉ። በመረጡት ሙያ ዘርፍ እንዲሰማሩ የሚያስችላቸው ስልጠናም ይሰጣቸዋል። እሷ በዚህ ዕድል ተጠቅማ በተለያዩ የእጅ ሥራዎች ትሳተፋለች። ሥራዎቿን ለውስጥና ለውጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሽጣ



**የህግ ታራሚ ሣራ ተሰማ፣**

የምትጠቀምበትም ሁኔታ ተመቻችቶላታል። ራሷንም ትደጉማለች። በበዓላት ወቅት ስጦታ ትሰጣለች።

‹‹እንዲህ እንደ ጥምቀት ያሉት ዐውድ ዓመቶች ለእኛ ልዩ ናቸው›› ብላናለችም አስናቀች። ወደ ማረሚያና ማረፊያ ቤቱ የገባችው በ2006 ዓ.ም ነው። በነፍስ ግድያ 20 ዓመት ተፈርዶባት አባሪዋ ከነበረ የ23 ዓመት ፍርደኛ ጋርም ነው የገባችው። በመሆኑም በዚህ ቆይታዋ በርካታ በዓላትን ከቤተሰቦቿ በመለየት በማረሚያና ማረፊያ ቤቱ ውስጥ ለማሳለፍ ተገድዳለች።

ሴት ሆኖ በዓላትን በእስር ቤት ማሳለፍ እጅግ መከበዱንና እሷና ጓደኞቿ በዓላትን ከሌላው ሰው በተለየ ሁኔታ በጉጉት እንደሚጠባበቁም ትናገራለች። በዓላት ለእነሱ ታላቅ ደስታና ተስፋ ይዘው የሚመጡ የዕድል በረከቶች እንደሆኑም ታነሳለች።

ደስታቸው ተትረፍርፎ ከሚቀርበው ምግብና መጠጥ በስተጀርባ ካለው ተስፋ ጋርም በእጅጉ ተሰናስሎ የተቆራኘ እንደሆነ አበክራ ትገልፃለች አስናቀች። እሷ እንደነገረችን ማረሚያ ቤቱ በየዐውድ ዓመቱ በማረፊያ ቤቱ ላሉ ሴት ታራሚዎች ምህረት ያደርጋል። ከምግብ መጠጡ፤ በዚሁ ከታጀበው ሞቅ ደመቅ ያለ ዝግጅትና ሀዘንን ከሚያስረሳው የበዓል ጨዋታና ደስታ በስተጀርባ ያለው ተስፋ በምህረት ወይም በይቅርታ ከስር መለቀቅ ነው።

ሁሉም ሴት ታራሚዎች ይሄን ሁሌ ዐውድ ዓመት በመጣ ቁጥር በጉጉት ይጠብቁታል። ዐውድ ዓመት ሲመጣ ደስ ደስ የሚላቸውና በዝግጅት ተፍ ተፍ የሚሉትም በዋንኛነት ለዚሁ ነው። ይሁንና ይሄ በይቅርታ ወይም በምህረት ከእሥር የመፈታት ተስፋዋ እስከ አሁን ዕውን አልሆነም። በማረሚያ ቤቱ ያሉት ጓደኞቿም እንዲሁ።

ከዘጠኝ ዓመታት በላይ በማረሚያ ቤቱ በእስር ያሳለፈችው አስናቀች ሁሉንም ዓመታት ያሳለፈቻቸው በተስፋና በበዓሉ ዝግጅት ድምቀት ነው። በተለይ በዘንድሮ የገና እና የጥምቀት በዓል በይቅርታ እፈታለሁ የሚል ተስፋዋ በብርቱ አይሎ ነበር። አንደኛው ምክንያቷ አሁን ባለችበት ሁኔታ ከተፈረደባት የእስራት ዘመን ሁለት ሦስተኛውን ለመፈፀም መብቃቷ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ወደ ማረሚያ ቤቱ እንድትገባ መንስኤ ከሆናት ሟች ዘመዶች ጋር በገዳ ስርዓት መሰረት ይቅር መባባሏ ነው። እንደምትለው ዘመዶቹ ጉማ ወይም ካሳ በልተናልና ይህችን ልጅ አንፈልጋትም ብለዋል። ሆኖም የገዳ ስርዓት ሕጉ ተጣጥመው የሚሄዱበት ስርዓት ስላልተዘረጋ ይቅርታውን ማግኘት አልቻለችም። ወደፊት ግን እንዲህ ያሉት የፍትህ ስርዓቶች ከህጉ ጋር በሚስማማ መልኩ ተቀባይነት ኖሯቸው ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚልም አስተያየት አላት ። አስናቀችም ሆነች ሌሎቹ ሴት ታራሚዎች ለዚህ ማረሚያ ቤቱን ተጠያቂ ሲያደርጉ አይደመጡም።

‹‹ማረሚያ ቤት ከእግዚአብሔር በታች አባታችንም እናታችንም ቤተሰባችንም ነው›› የምትለው የህግ ታራሚ ሣራ ተሰማ በማረሚያና ማረፊያ ቤቱ በ2007 ዓ.ም ገብታ እስካሁን የቆየችው ሣራ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ኬንያ ላይ ተይዛ ነው በፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቷ ተረጋግጦ ወደ ማረሚያ ቤቱ ልትገባ የቻለችው።

‹‹ከሰው ስህተት ክብረት ዝገት አይጠፋም›› እንደሚሉት ተረት በእርግጥ አጥፍቻለሁ። ሆኖም ስህተቴን አምኜ ተቀብያለሁ። የምትለው ሣራ በየዓመቱ



**የህግ ታራሚ አስናቀች ጌታቸው፣**

ምህረት ይደረግልኛል ብላ በተስፋ ስትጠባበቅ መቆየቷንም ታወሳለች። ይሄን በየዓመቱ መጠባበቅ የእሷ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሴት ታራሚዎች ብርቱ ፍላጎት መሆኑንም ታነሳለች።

‹‹በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ድሮ የነበረኝ አስተሳሰብ ዛሬ ላይ አለመኖሩን ነው›› የምትለው ሳራ በቆይታዋ ከበቂ በላይ ከስህተቷ በመታረሟ ነገ ከራሷ አልፋ ለቤተሰቧና ለህብረተሰቡ የተሻለ መልካም ነገር የምታደርግ መሆኗንም በራስ በመተማመን መንፈስ ታወሳለች። ስለዚህም በየዓመቱ የሚለጠፈውን የይቅርታ ዝርዝር በጉጉት እንደሚጠብቁ ሴት ታራሚዎች በጉጉት መጠበቋን አላናግር ብሎ የሚተናነቃት እንባ ከዓይኖቿ በመፍለቅ በጉንጯ ላይ እየተዝረከረከ ትገልፃለች።

‹‹ቢሆንም ከዓመት ዓመት ይቅርታ ባለማግኘታችን እናትም አባትም ሆኖ ከነልጆቻችን በቀን ሶስቴ የሚቀልበንን ማረሚያ ቤት ተጠያቂ አናደርግም›› ትላለች። እንደምትለው ማረሚያ ቤቱ የተሰጠውን ሕግ ነው የሚያስፈፅመው። እንደውም የሕግ አማካሪ ቀጥሮ ሁሉ ይቅርታ ይጠይቅላቸዋል። ይግባኝ ሁሉ እንዲጠይቁም ያደርጋል። ሰብዓዊ መብታቸውን በማክበርና በአያያዝ ረገድም እንከን የለሽ ነው።

ሲታመሙ አስታሞ ሲቸገሩ ተቸግሮ፤ ሲያለቅሱ አብሮ አልቅሶ ሲደሰቱ ተደስቶ አውድ ዓመትን በደስታ እንዲያሳልፉ በጀት መድቦ ይንከባከባቸዋል። ለነሱ ይቅርታ በመጠየቁ ጉዳይ ማረሚያ ቤት ምንም ማድረግ አይችልም።

‹‹ሴት ልጅ እንደወንድ አይደለችም ብዙ ችግሮች አሉባት›› የምትለው ሣራ አራት ልጆችና ቤተሰብ እንዳላት ከቅጣቷ አብዛኛውን በመፈፀሟ መንግስት ይሄን ከግንዛቤ በማግባት ከሕግ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለእሷና ለሌሎች ሴት ታራሚዎች ምህረት እንዲያደርግ በዐውድ ዓመት ስም ትጠይቃለች።

የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ መጋዘን ቁልፍ በእጇ ሆኖ በመዘረፉ በከባድ ዕምነት ማጉደል ምክንያት ነው ከአንድ ባልደረባዋ ጋር ተፈርዶባት ወደ ማረሚያ ቤቱ የገባችው። ቆይታዋና የዐውድ አመት ክብር ሰው መሆን ምንድነው፤ ሕይወት ምንድነው የሚለውን እንድትማር አስችሏታል።‹‹ ስወጣ አይደለም እኔ ቤተሰቤን መላው ማህበረሰብ ሁሉ ማስተማር እችላለሁ›› የመንግስት ጠበቃ ሲከራከርላት መቆየቱንና ቁልፍ ስለያዘች ተጠያቂ መሆኗን ደጋግማ የምታወሳው ታራሚዋ ለበዓላት እኛ ያየነውን ሞቅ ደመቅ ያለ ዝግጅት ቢያደርጉም እሷን ጨምሮ አብዛኞቹ በተለይም ደግሞ በማረሚያ ቤቱ 3 አራተኛ የእስራት ጊዜያቸውን የፈፀሙ በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ይቅርታ ሲያጡ ደስታቸው በለቅሶ ተለውጦ ዐውድ ዓመቱን በለቅሶ ጭምር የሚያሳልፉበት ጊዜ እንዳለና ሆኖም በየዓመቱ ምህረት ይደረግልናል በሚል በተስፋ እንደሚጠባበቁ አውግታናለች አስናቀች።

የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ቤት አባልና የሴቶችና ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ ቡድን መሪ ምክትል ኢንስፔክተር በዛብሽ ማርያም እንደሚሉት በማረሚያ ቤቱ 558 ሴት ታራሚዎች አሉ:: ለአውደ አመት በልዩ በጀት በግና በሬ በማረድ በዓላትን በደስታ እንዲያሳልፉ ይደረጋል ይላሉ።

የሕግ ታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት በማክበርና በማስከበር በኩል የይቅርታ አሰጣጥ ዋና ዓላማ የሕዝብ የመንግስትንና የታራሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል መንግስት ጥፋተኞች በጥፋታቸው



**የህግ ታራሚ አስናቀች ሞገሴ፣**




**ምክትል ኢንስፔክተር በዛብሽ ማሪያም፣**

የተፀፀቱና የታረሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ወደ ሕብረተሰቡ ተቀላቅለው አምራችና ሕግ አክባሪ ዜጋ ማድረግ ነው። አመክሮ አንድ የሕግ እስረኛ የእስራት ቅጣት ተወስኖበት ከእስራት ዘመኑ ሁለት ሦስተኛውን እንደፈፀመ የጠባዩ መሻሻል በበቂ ሁኔታ ሲመሰከርለት ከእስር ቤት እንዲፈታ የሚፈቀድበት ሁኔታ ነው። ይህም ሲባል በሕጉ የተወሰነው የአፈፃፀም ጊዜ ሲደርስና ጠቅላላ ሁኔታው ተሟልቶ ሲገኝ ጥፋተኛውን በአመክሮ አስቀድሞ መልቀቅ የሚቻል መሆኑን ያመለክታል። አመክሮ ጠባይ ማሻሻያና ወደ ማህበራዊ ኑሮ መመለሻ መሣሪያ ነው። ከዚህ አኳያ አመክሮ የሚፈቀደው እስረኛው በጠባዩም ሆነ በጠቅላላ ሁኔታው የተሻሻለ መሆኑ ሲታመን ነው። የአመክሮ ጊዜ አንድ የሕግ እስረኛ የተበየነበት ረጅም የእስራት ጊዜ ከማለቁ በፊት ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ከአደገኛ ጥፋትና የወንጀል ድርጊት ተገትቶ የመልካም ስነ ምግባር ተገዢ ሆኖ ይኖር እንደሆነ የሚፈተሽበት ወቅት ነው።

በእስራት የተቀጣን የሕግ እስረኛ በአመክሮ ለመልቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 207 የሕግ እስረኛው ከተፈረደበት የእስራት ዘመን ሁለት ሦስተኛውን መፈፀሙን፤ እስረኛው በማረሚያ ቤት በነበረበት ጊዜ መልካም ጠባይ ያሳየ በመሆኑ በቂና አጥጋቢ የምስክር ወረቀት ማግኘቱ፤ እስረኛው ከማረሚያ ቤት ሲወጣ ሥራ የሚያስገኝ መሆኑ መረጋገጡ እስረኛው በተቀጣበት የወንጀል ክስ ከባላጋራው ጋር እርቅ መፈፀሙ ይታያል መሰየም ወንጀለኞች ከስር ከተለቀቁ በኋላ መልካም ስማቸውን የሚያስመልሱበት መንገድ ነው። አንድ ወንጀለኛዋ የቀድሞ መልካም ስሟን የሚያስከብርላትና የጥፋተኛ ስሟ የሚፋቅበት መንገድ ነው። ውጤቶቹም በቀጥታ የነበረችው ሴት ከተሰየመችበት ጊዜ ጀምሮ ተወስኖባት የነበረው የሙብት፤ የማዕረግ ወይም የችሎታ ማጣት ቀሪ በማድረግ ሕዝባዊ መብቱን ቤተሰብ የማስተዳደርና የሙያ ሥራ የመሥራት መብቱን እንደገና ለመያዝ ችሎታ የምታገኝበት አግባብ ነው። በተጨማሪም የምትሰየም ሴት ቀድሞ የተላለፈባት ቅጣት ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ እንዲፋቅና ወደፊትም እንዳልተፈረደባት እንዲቆጠር ሕጉ ታሳቢ እንደሚያደርግ ይናገራሉ። በመሆኑም በማናቸውም ጊዜ በዚህች ግለሰብ ላይ ያለፈውን ወንጀል አንስቶ መውቀስ ስም ማጥፋትና ሌሎች ድርጊቶችን መፈፀም ክልክል ናቸው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን በ1960ዎቹ የታተሙ ጋዜጦችን ዘገባ ያስታውሰናል፡፡ በወቅቱ በአንጋፋው ጋዜጣ አዲስ ዘመን ከታተሙ ዘገባዎች መካከል ማጭበርበር፣ የትራፊክ እና የንግድ ሥርዓት መጣስ እንዲሁም ልማት ተኮር ዜናዎች ይገኙበታል፡፡ አንዳንዶቹ ዘገባዎች ዝርዝር መረጃ በደንብ የሌላቸው ናቸው፡፡ መግቢያው ዜና ላይ የሚናገረው የገንዘብ መጠንና ማጠቃለያው ዜና ላይ የሚጠቀሰው የገንዘብ መጠን የሚለያይበት አለ፡፡ ከዚህ ባሻገር የናይጄሪያው ቢያፍራን አስመልክቶ የወጣው ዘገባ ቀደም ሲል በወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ከተማ ይፍሩ የእርስ በርስ ጦርነቱን ለማስወገድ ያደረጉትን የእርቅ አውርድ ጥረት አስመልክቶ የሚያስታውሰን ነገር አለ፡፡

### ስማኙ ታሰረ

ድሬዳዋ (ኢ-ዜ-አ-)፤ ጌታቸው ኃይሉ የሚባለው ሰው ሙሉ ጤንነት እያለው በሽተኛ ነኝ እያለ በመሬት እየተንፏቀቀ ሲለምን ተገኝቶ ድሬዳዋ ፫ኛ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ የፈጸመው ወንጀል በማስረጃ ስለተረጋገጠበት በስድስት ወራት እስራት እንዲቀጣ ተፈረደበት ፡፡

ጌታቸው ኃይሉ ስሙን በመለዋወጥ ጀማል ኢሳ በመባል እየተጠራ ጤናማ ሆኖ ሠርቶ መኖሩን ጠልቶ የሆቴል ቤት እየተዘዋወረ በመለመኑ ሰውን ያስቸገረ እንደነበረ ሕግ አስከባሪው የሃምሳ አለቃ ከበደ ካብትህ ይመር ገለጡ፡፡

(ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

### በሞተር የሚሠራ የኤሌክትሪክ መብራት ለማሠራት ብር አዋጡ

የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት የጢቾ አውራጃ ሕዝብ ፲፫ ሺ ብር በማዋጣት በሞተር ኃይል የሚሠራ የኤሌክትሪክ መብራት ለማቋቋም ተስማማ፡፡

ኅዳር ፯ ቀን በወረዳው ገዥ ይኩኖ አምላክ ኃይለ ማርያም አማካይነት በሕዝቡ ፴፩ሺህ ብር የተዋጣ መሆኑን አቶ ፈቃደ ወንድሙ ገለፁ፡፡

(ጥቅምት ታኅሣሥ ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

### ዋጋ ያስበለጡ ተቀጡ

ጅማ፣ዲላ (ኢ-ዜ-አ-) ፤ በከፋ ክፍለ ሀገር በሶኮሩና በመሐል ማጂ ወረዳዎች ኗሪ የሆኑ አራት ነዋሪዎች ከተወሰነው ዋጋ በላይ ጨው ሲሸጡ በመገኘታቸው ተከሰው በጠቅላላው ፮፻፫ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ተፈርዶባቸዋል፡፡

ከተከሳሾቹ መካከል በ፲፫ ብር ከ፵ ሳንቲም መሸጥ የሚገባቸውን አንድ ቁምጣ ጨው ከ፳፰ እስከ ፴ ብር ሲሸጡ የተገኙት አቶ ናጂ አሊ ፫፻ ብር ሲቀጡ ፤ አቶ መሐመድ ጀማልም ተመሳሳይ ጥፋት በመፈጸማቸው ፪፻፵ ብር መቀመጫ እንዲከፍሉ ፤ ባይከፍሉ ግን ፴፰ ቀናት እስራት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው መሆኑን የየወረዳው ፍርድ ቤት ዳኞች ገልጠዋል፡፡

እንዲሁም አቶ አደም መሸሻና አቶ የሱፍ ትኩዬ የተባሉት ነጋዴዎች ፤ በመሐል ማጂ ወረዳ አንድ አሞሌ ጨው ከዋጋው አስበልጠው ፫ ብር ሲሸጡ በመገኘታቸው ተከሰው አድራጎታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ፤እያንዳንዳቸው ፵፫ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ የዲላ ወረዳ ፍርድ ቤት ሰሞኑን በዋለው ችሎት በይኖበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ሰሎሞን በርሔ የሕዝብ ማመላለሻ ሹፌር ከማዘጋጃ ቤት የሚጠየቀውን ግብር ላለመክፈል ሲል ለሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች መነሻና መድረሻ ከተከለከለው ሥፍራ ውጭ ሕዝብ ሲያሳፍርና ሲያወርድ በመገኘቱ ፵ ብር መቀጫ እንዲከፍል የዲላ ወረዳ ፍርድ ቤት ሰሞኑን ባዋለው ችሎት በይኖበታል፡፡

ተከሳሹ ቅጣቱ የተበየነበት መንገደኞችን ከአዋሳ ከተማ ዲላ ካደረሰ በኋላ ለመነሻና መድረሻ በተከለለው ሥፍራ በማውረድ ፋንታ ፤ መንገደኞቹን ባልተለመደበት ቦታ ደብቆ ሲያወርድ፤ ሌሎችንም ሲያሳፍር መገኘቱ በማስረጃ ስለተረጋገጠበት ነው፡፡

ሰሎሞን ከአሁን በፊትም ለመኪናዎች መነሻና መድረሻ ከተከለለው ቦታ አላቆምም በማለቱ ተከሶ ፲፫ የተቀጣና ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶት እንደነበር ተገልጧል፡፡

ከዚህም ሌላ ዋለልኝ ደሚ የተባለው የከባድ የጭነት መኪና ሹፌር አለደረጃው የ፫ ደረጃ መንጃ ፈቃድ ይዞ በመገኘቱ ይኸው ፍርድ ቤት የ፵ ብር ቅጣት የበየነበት መሆኑን የደራሳ አውራጃ ፖሊስ ትራፊክ ሹም የአስር አለቃ ነጋሽ አብዲ ገልጠዋል፡፡

(ጥቅምት ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

### ቢያፍራ መነጠል የለባትም

**የኮንጎ ፕሬዚዳንት**

ብራዛቪል ፤(ኤ-ኤፍ-ፒ-) የኮንጎ ብራዛቪል ፕሬዚዳንት ማጀር ማሪየን ኑጉዋቢ ፤ቢያፍራ የሚለው ቃል ከክፍለ ዓለማችን ውስጥ ጨርሶ መጥፋት አለበት በማለት፤ ፌዴራል ናጄሪያን የሚደግፉ መሆናቸውን ትናንት በይፋ ማስታወቃቸው ተገለጠ፡፡

ማጆር ንጉዋቢ ይህን መግለጫ የሰጡት ፤አዲስ አበባ ተደርጎ ከነበረው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ ሲመለሱ መሆኑ ታውቋል፡፡

**መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )**

# ዓለም አቀፍ



የአልሸባብ ታጣቂዎች

## አሜሪካ 30 የአልሻባብ ታጣቂዎች መግደሏን አስታወቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ የሶማሊያ መንግሥት በአልሻባብ ላይ እያካሄደ ላለው ዘመቻ ለመደገፍ በፈጸመችው የአየር ጥቃት 30 የሚደርሱ የአልሸባብ ታጣቂ ቡድን መግደሏን አስታወቀች፡፡

ጥቃቱ የተፈጸመው ከሶማሊያ ዋና ከተማ ሞቃዲሾ በስተሰሜን ምሥራቅ 260 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ጋልካድ በተባለች ከተማ አቅራቢያ ሲሆን ባለፉት ጥቂት ቀናት የሶማሊያ መንግሥት ሠራዊት እና የአልሻባብ ታጣቂዎች ከተማዋን ለመቆጣጠር ሲዋጉ ቆይተዋል።

ከጥቃቱ ቀደም ብሎ እስላማዊ ታጣቂዎቹ ጋልካድ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ወታደራዊ ሰፈር ላይ ጥቃት ፈጽመው ሰባት የመንግሥት ወታደሮችን መግደላቸዉን የሶማሊያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር እናዳለው ገልጸዉ፤ከጥቃቱ ጋር ተያይዞ በርካታ የአልሻባብ ታጣቂዎች መገደላቸውን አስታውቀዋል፡፡

አልሻባብ በሶማሊያ ውስጥ ጽንፈኛ እስላማዊ መንግሥት ለማቋቋም አላማ ይዞ ከ15 ዓመት በፊት ጀምሮ በእርስ በርስ ጦርነት የተዳከመውን የሶማሊያን ማዕከላዊ መንግሥት ለመጣል ሲዋጋ የቆየ ሲሆን ቡድኑ ከዋና ከተማዋ የሞቃዲሾ አካባቢዎች በኃይል ተገፍቶ የወጣ ቢሆንም ወታደራዊ እና የሰላማዊ ሰዎች አካባቢዎችን ኢላማ በማድረግ ከባድ ጉዳትን እያደረሱ ያሉ ጥቃቶችን እየፈጸመ ይገኛል።

የሶማሊያ መንግሥት እና የጎሳ ሚሊሻዎች ባለፉት ወራት በታጣቂ ቡድኑ ላይ በጥምረት እያካሄዱት ባለው ዘመቻ ምክንያት ቡድኑን ከበርካታ ቦታዎች እያስለቀቁት ይገኛሉ።

ባለፈው ሰኞ የሶማሊያ መንግሥት እንዳስታወቀው የአገሪቱ ሠራዊት እና የአካባቢ ሚሊሻዎች ሃራርድሄር የተባለች የወደብ ከተማን ለመቆጣጠር ችለዋል። ከተማዋ ከ2010 የአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ጀምሮ የአልሻባብ የተለያዩ አቅርቦቶች ቁልፍ ቦታ ሆና መቆየቷ ተነግሯል።

በአፍሪካ የአሜሪካ ወታደራዊ ዕዝ በጋልካድ አቅራቢያ ላይ ስለተፈጸመው ጥቃት ባወጣው ሪፖርት ላይ እንዳመለከተው ሦስት የአልሻባብ ተሽከርካሪዎች በጥቃቱ ወድመዋል። ዕዙ ጨምሮም በአየር ጥቃቱ “በሰላማዊ ሰዎች ላይ ምንም አይነት ጉዳትም ሆነ ሞት አለመከሰቱን” አመልክቷል። ነገር ግን ስለተፈጸመው የአየር ጥቃት ዝርዝር ሁኔታ ከገለልተኛ ወገን የተሰጠ ማረጋገጫ የለም።

“ትልቁን እና አደገኛውን የአልቃኢዳ አጋር የሆነውን አልሻባብን ለመደምሰስ ለሚዋጉ ኃይሎች በአፍሪካ የአሜሪካ ዕዝ የሚያስፈልጋቸውን የሥልጠና፣ የምክር እና የቁሳቁስ ድጋፍ መስጠቱን ይቀጥላል” ብሏል የአሜሪካ ሠራዊት ባወጣው መግለጫ።



አምባሳደር ሊንዳ ቶማስ-ግሪንፊልድ

## በተመድ የአሜሪካ አምባሳደር ዳግም አፍሪካን ሊጎበኙ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በተባበሩት መንግስታት የአሜሪካ አምባሳደር ሊንዳ ቶማስ-ግሪንፊልድ በፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አማካኝነት ዳግም አፍሪካን ሊጎበኙ መሆናቸውን ቢቢሲ ዘገበ፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአሜሪካ ሚሲዮን እንዳስታወቀው አምባሳደር ሊንዳ ቶማስ-ግሪንፊልድ ከፈረንጆቹ ጥር 25 ጀምሮ ወደ ጋና፣ ሞዛምቢክ እና ኬንያ የሚጓዙ ሲሆን ጉዞው ከዋና ዋና የአሁን እና የቀድሞ የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት አባላት ጋር አሜሪካ ያላትን አጋርነት ለማረጋገጥ እና ለማጠናከር ያለመ መሆኑ ተነግሯል።

የቶማስ-ግሪንፊልድ ጉብኝት ባለፈው ሳምንት በግምጃ ቤት ፀሐፊ ጃኔት የለን የተደረገን 10 ቀናት የአፍሪካ ጉብኝት የተከተለ መሆኑንና ባይደን በታኅሣሥ ወር የአሜሪካ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ መገባደጃ ላይ በፈረንጆች 2023 ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራትን እንደሚጎበኙም መግለጻቸው ይታወሳል።

በአፍሪካ ቻይና በንግዱ አሜሪካን በበለጠችበት እና የጦር ኃይሏን ለመጨመር እየተንቀሳቀሰች ሲሆን፤ ሩሲያ ደግሞ ከማሊ እና ከመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ ባለስልጣናት ጋር ወታደራዊ ግንኙነት አላት።

ከጥር 26 እስከ 27 በጉብኝታቸው ወቅት የአሜሪካ ሚሲዮን ከተመድ ባለስልጣናት፣ ስራ ፈጣሪዎች፣ ከአሜሪካ ልውውጥ የቀድሞ ተማሪዎች፣ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ተማሪዎች እና አየር ንብረት ለውጥ ላይ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ጋር እንደሚገናኙ ተገልጿል።

ከጥር 28 እስከ 29 የአምባሳደሯ የመጨረሻ ማረፊያ ኬንያ መሆኑም ታውቋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

## የማይበጠሰው

ከብርሃኑ ተሰማ/አዲስ አበባ/

“የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሰማዩ ላይ ሲታይ እልልታው ቀለጠ” የሚለው ከሰሞኑ ከመቀሌ የተሰማው ዘገባ የአንድ አገር ዜጎች ተነፋፍቀው እንደነበር የሚያመላክት ሁነኛ ማሳያ ነው። ባልተፈለገና ባልተጠበቀ ሁኔታ ተለያይተው የቆዩት የአንዲት አገር ሰዎች ወደ ሌላው የአገራቸው ክፍል ሲሄዱ የታየው ደስታ በራሱ ያስደስታል።

የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትና የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሮች ልዑካን ቡድን ወደ ሰሜኗ አብሪ ኮከብ ከተማ መቀሌ ሲደርሱ ወገናቸውን የናፈቁት የከተማዋ ነዋሪዎች የአገር ዓርማ አንግቦ በዓለም ዙሪያ የሚዘዋወረው ሰንደቅ ዓላማቸውን ያነገበ አውሮፕላን በአየር ላይ ማየታቸው በራሱ ያልተበጠሰውና የማይበጠሰው ኢትዮጵያዊነት ዛሬም መቀጠሉ አሳይቷል።

አውሮፕላኑ ካረፈ በኋላ የተከተለውን የቡድኑ አባላትና በመቀሌ አሉላ አባነጋ ኤርፖርት የነበሩት አስተናጋጆቻቸው ሲተቃቀፉና ሲሳሳሙ ያየ የተገናኙት በተለያዩ ምክንያቶች ተራርቀው የቆዩ የአንድ ቤተሰብ አባላት እንጂ፤ ለሁለት ዓመታት ያህል በተቃራኒ ጎራዎች ተሰልፈው ሲፈላለጉ የቆዩ ወገኖች አይመስሉም። የልዑካን ቡድኑ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስም የነበረው ስሜት ተመሳሳይ ነበር።

### የቀጠለው

የልዑካን ቡድኑ ጉዞ ተከትሎ 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ የቀጠለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአዲስ አበባ መቀሌ በረራም ቤተሰቦችን ዳግም ያገናኘና በዚያ ፍጥነት ሊደረግ ይቻላል ተብሎ አልታሰበም።

ይህኛው ደግሞ እስከ 20 ወራት ለዘለቀ ጊዜ ተለያይተው የቆዩ ባልና ሚስትን፣ ወላጆችና ልጆችን እንዲሁም የአንድ ቤተሰብ አባላትን ያገናኘ ክስተት ሆኗል። ማንና መቼ እንደሚመጣ ባልታወቀበት ሁኔታ ድንገት ያገናኘ።

በፖለቲከኞችና በአገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮች የተጀመረው ግንኙነት አትሌቶችን አስከትሏል። በቀጣይም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማካተት ወደ መደበኛው ግንኙነት ይመለሳል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

በረራዎቹ ኢትዮጵያውያን በተፈጠረው ችግር ሳይገናኙ ተራርቀው እንደሆን እንጂ፤ እንዳልተለያዩም አመላክቷል።

እምብዛም ሳይቆይ አገልግሎት የቀጠለው የስልክ አገልግሎት ደግሞ ራቅ ካሉት ወገኖች፣ ዘመዶችና ጓደኞሞች ማገናኘት እያስቻለ ነው። በአካል መገናኘት እስከሚቻል ድረስ በድምፅና በጽሁፍ መልዕክቶች ሰላምታን ማድረስ ህልውናን ማረጋገጥ አስችሏል።

ሰብዓዊ ድጋፍን አስቀድሞና ኤሌክትሪክን አስከትሎ ወደ ትግራይና አጎራባች ክልሎች እየዘለቀ ያለው መሠረታዊ አገልግሎት የጎደለው በሂደት እንደሚሟላ መንገድ አሳይቷል። በአገር ደረጃ የሚታዩ ችግሮች በመኖራቸው ሁሉም ነገር በአንዴ እንደማይሟላ ማሰብም ተገቢ ይሆናል።

### ትናንት

አገር መርተው አገርን የወጉ፣ አንድነቷን ማስጠበቅ ሲገባቸው፤ በአንድነቷ ላይ የመጡ፤ ጠላቶቿን መመከት ሲገባቸው፤ ጠላትን የተባበሩ አጋጥመውናል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ለአገር ጋሻና መከታ የሆነች አንዲት አገር ዋስና ጠበቃ መሆን ሲገባቸው መራራቅን ሲሰብኩ የነበሩ ዜጎች ገጥመውናል።

የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት፣ የአክራሪና ጽንፈኞች በጥባጭነትና ድንጋይ አቀባይነት ታክሎበትም በአገራችን የተፈጠረውን ግጭት ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ለመውሰድ ጥረት ሲደረግም ቆይቷል።

በተለይ በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ዳያስፖራዎች ብሄርን እንጂ፤ አገሩን የሚጠላ ዜጋ ለመፍጠር ያደረጉት መንፈራገጥ አሳፋሪ ሆኖ በታሪክ መዝግቦታል።

በአንዲት አገር የሚኖር ከመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ በተያያዘና የጋራ አገር ዋልታና ማገር የሆኑ ትውልዶች እምነት፣ ባህልና ታሪክ ያስተሳሰረው ኩሩ ሕዝብ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በጦርነት ውስጥ ለመቆየት ተገዶ ቆይቷል።

ከጠብመንጃ አፈ ሙዝ እሳት እንጂ፤ ምግብ ስለማይወጣ የሚመገቡት በማጣት፡ ከመድፎችና ላውንቸሮች የሚተኮሰው መድኃኒት ሳይሆን፤ ወላፈን በመሆኑ የታመሙትን ማከም አዳጋች ነበር።

በጦርነት ቀጣና ውስጥ ለሚኖረው ሕዝብ መሠረታዊ አገልግሎት ለማቅረብ አስቸጋሪ በመሆኑም ኑሮን ከባድ አድርገውበታል። ሌላው ቀርቶ በገዛ ገንዘቡ የሚገዛው በማጣት የተጎዳ ቀላል አይባልም።

በትግራይ ክልል የታዩት ችግሮች በአማራና በአፋር ክልሎችም መጠኑ ይለያይ እንጂ አጋጥመዋል። ሕዝቡ በጦርነቱ ሕይወትን መገበር ጨምሮ ያላየው መከራ አልነበረም ማለቱ ይቀላል።

ልዩነቶችን ባልሰለጠነ መንገድ ለመፍታት የተከፈተው ጦርነት ሁላችንንም ጎድቶናል። የጉዳቱን ዓይነትና መጠን ለመዘርዘር ጊዜ የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ለመገመት ግን አያዳግትም።

### ዛሬ

በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በኬንያና በደቡብ አፍሪካ በተደረጉት ድርድሮች የሰላም በሮች ተከፍተዋል። በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተስፋ አሳይቷል። በአተገባበሩ ዙሪያ አልፎ አልፎ የሚሰማ አደፍራሽ ነገር ባይታጣም።

በስምምነቱ መሠረት በተከታታይ ወደ ትግበራ የሚገቡትና ተጨማሪ ድርድር የሚፈልጉ ጉዳዮች ለይቶ መተግበር ከስምምነቱ ተፈራራሚ አካላት ይጠበቃል ። ታጥቦ ጭቃ መሆን የለበትም።

### ድርድሩ የደረበው

ቀድሞውንም መነጋገርና መደራደር የራቀውን የኢትዮጵያውያን ግንኙነት በአፍሪካ ኅብረት የተጀመረው ድርድር ጉልበት ጨምሮለት “እኛ ለእኛ አናንስም” ወደሚል ሌላ አኩሪ ምዕራፍ ተሸጋግሯል።

“የምን ደቡብ አፍሪካ፤ የምን ኬንያ ችግሮቻችንን የምንፈታው በገዛ አገራችን ነው” የሚል አስተሳሰብ በመያዝ የሚፈለግ፣ የሚጠበቅና መሆን ያለበት አቋም የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት ከኢትዮጵያውያን በላይ ማንም፤ ከኢትዮጵያም የተሻለ ቦታ እንደሌለ አሳይቷል።

### በቀጣይ

ከትምህርት ገበታ ርቀው በቤትና በሌሎችም ቦታዎች የዋሉ ሕጻናትና ወጣቶች ትምህርታቸውን መቀጠል ይገባቸዋል።

በትግራይ ክልል የሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /ዩኒቨርሲቲዎች/ጨምሮ ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርት ተቋማት ሥራ መጀመር አለባቸው።

በተጨማሪም ሕዝብ አገልግሎት የሚፈለግባቸው መንግሥታዊ ተቋማት ሥራ ማስጀመር ያስፈልጋል።

የትግራይ ክልል ከከተሞቹና ከወረዳዎች ጋር የሚያገናኙ የትራንስፖርት መሥመሮች መከፈት አለባቸው። ከዚያም የትራንስፖርት አገልግሎት ከአጎራባች ክልሎችና ወደ መሃል አገር በማስቀጠል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነት ነፍስ መዝራት ይጠበቅበታል።

በክልሉ ጦርነቱ የተጎዱትንና የወደሙትን ተቋማትን በመጠገንና መልሶ ማቋቋምም ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆንም አለበት።

ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሰላምና የጋራ ልማት ኮንፍረንሶች በማድረግ የሰላም ግንባታ መጀመር ተገቢ ይሆናል።

በፌዴራል መንግሥትና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር አወዛጋቢ በተባሉ ጉዳዮች ላይ ፖለቲካዊ ድርድሮችን በማካሄድ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሄ መስጠት ይገባል።

ለዘላቂ ሰላምና ዕድገት እርቅና ይቅርታ አስፈላጊነትን ማሰብም ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ቢሆን መልካም ነው።

በአገር ደረጃ የተቋቋመው አገራዊ ምክክር ኮሚሽን በክልሉ ሥራ የሚጀምርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው። በዚህም ዳግም ወደ ጦርነትና ደም መፋሰስ የሚያስገቡ ችግሮች መቼም እንዳይከሰቱ ማድረግ ያስፈልጋል።

> **ከጠብመንጃ አፈ ሙዝ እሳት እንጂ፤ ምግብ ስለማይወጣ የሚመገቡት በማጣት፡ ከመድፎችና ላውንቸሮች የሚተኮሰው መድኃኒት ሳይሆን፤ ወላፈን በመሆኑ የታመሙትን ማከም አዳጋች ነበር**

ምክክሩ በተለይ በክልሉ ኢትዮጵያውያን ባልሰለጠነ መንገድ በመጓዝ በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ከሚያሳፍራቸውና ከሚያሸማቅቃቸው የጦርነት አባዜ በመውጣት ችግሮቻችን በውይይትና በመነጋገር መፍታት እንደምንችል ለዓለም ምናሳይበት ወቅት ነው።

ክልሉ በአገራዊና ክልላዊ የልማት ሥራዎች ተሳትፎውን ማጠናከር አለበት። በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በሌሎች ዘርፎች በስፋት መንቀሳቀስ መጀመር አለበት።

ክልሉ በተለይ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ያሳየውን ሞዴል በአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ በማጀብ የሰው ልጆች ህልውና ስጋት የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ሚናውን መጫወት ይጠበቅበታል።

### ኢትዮጵያዊነት

ትግራይን ያላካተተ ትናንት አልነበረም፤ ዛሬም የለም፤ ነገም አይፈጠርም። ባለፉት ሁለት ዓመታት በተፈጠሩ ችግሮች የዚህ ኩሩና ነጻነቷን አስከብራ የኖረች አገር ዜጎች መሆናችንን ለጥያቄ ሊቀርብ አይገባም።

የኢትዮጵያ መሠረቶች አንዱ የሆነው ትግራይ አገራዊ አንድነትን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ጥረቱን ማጠናከር አለበት።

ኢትዮጵያዊነትን ለድርድር የማያቀርብ አስተማማኝና ዘላቂ አገራዊ አንድነትን ማጠናከር ዋነኛው ተግባር መሆን ይገባዋል። ያለመተማመንና ጥርጣሬ መኖር የለበትም።

ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድና በአህጉሩ ሞዴል ሆና እንድትቀጥል ሚናውን መጫወት ይጠበቅበታል።

### ኢትዮጵያውያን

ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት የጋራ ርብርብ በማድረግ በደም የተሳሰረውን፣ ያለውን የሚያካፍለውን፣ በኀዘንና በደስታ የማይለያየውን፣ ድህነትና ኋላ ቀርነት የታገለው ሕዝብ የአንድነትና የአብሮነት የማይበጠስ ግንኙነት ማጠናከር ይገባናል።

በተለይ በትግራይ ክልል የሚገኙ ወገኖቻችን ባልተፈለገ መንገድና በማይጠበቅ ሁኔታ ችግር ውስጥ ቆይተዋል። የአማራና የአፋር ክልሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። እናም በችግር ውስጥ የቆየውን ሕዝብ ለመርዳትና የወደሙና የፈራረሱ ለማቋቋምና መልሶ ለመገንባት ዋነኞቹ ባለቤቶች እኛ ስለሆንን ክንዳችን አስተባብረን መነሳት አለብን።

የውጭ መንግሥታት ዓለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ የማይናቅ ቢሆንም፤ የራሳችን አቅም በማስተባበር ታሪክ መሥራት ስለሚቻል።

ትናንት ስንጣላ ዱላ ያቀበሉ ወገኖች መቼም የምንገናኝ ስላልመሰላቸው ሊያለያዩን ሞክረው ዳር ቀርተዋል ስንታረቅ ደግሞ ተደንቀዋል፤ ተገርመዋል፤ አፍረዋል።

ታዲያ ፕሪቶሪያ የተደረሰው ስምምነት ዓለምን በማስደነቅ ኢትዮጵያውያን የማንነጣጠል መሆናችንን አሳይተናል። ስምምነቱን ተከትሎ የተከናወኑ ተግባራትም አድናቆትና አጀብ ማሰኘታቸውን ቀጥለዋል።

ይህንን በዘመናችን እየተመዘገበ ያለውን ድንቅና አስገራሚ ታሪክ በዳግም ግንባታና በመልሶ ማቋቋም በመድገም ኢትዮጵያውያን ዛሬም አንድነታችንን ማሳየት ይጠበቅብናል።

“የዘመድ ጥል፤ ከሥጋ ትል” እንዲሉ “ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን፤ ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለቅም” እንደተባለውም በመደማመጥና በመግባባት እንኳን የአገራችንን የሌሎች አገሮች ችግሮችንና ቀውስ መፍታት እንችላለን። ጎረቤቶቻችን ችግር ውስጥ ሲወድቁ ማግባባት እንደቻልንም ማስታወስ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲል ብቻ ሳትሆን፤ በመልካም ተግባራት እንቅስቃሴዋ የአፍሪካ ሞዴል ሆና መቀጠል እንደምትችል በተግባር ታሳያለች።

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የሥጋ ደዌን በሽታ - አሁንም እንዘንጋው!

ዓለማየሁ ማሞ

ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ለአካል ጉዳት ተጋላጭ ናቸው። ማንም ሰው አካል ጉዳተኛ ላለመሆን ዋስትና የለውም የሚባለውም አካል ጉዳተኝነት በሁሉም ሰው ላይ በድንገት ሊከሰት የሚችል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የአካል ጉዳተኝነት አምራች ዜጋ በመሆን ለሀገር በጎ ከመስራት በምንም መልኩ ሊያግድ አይችልም። በዚህ መሰረት አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው ተገቢውን የትምህርትና የሥልጠና ዕድል ካገኙ ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ።

በአካል ጉዳተኞች መብቶች (CRPD) ሰነድ ውስጥ አካል ጉዳተኝነት በሁሉም መልኩ መከበር እና መደገፍ ያለበት መሆኑን እና የሰው ልጅ ብዝሃነት ተፈጥሯዊ አካል መሆኑን፣ አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው በሕብረተሰብ ውስጥ ያሉ መብቶች እንዳላቸውና የአካል ጉዳት (እክል) የሰዎችን መብት ለመከልከል ወይም ለመገደብ እንደ ሰበብ መጠቀም እንደሌለበት ተደንግጓል። በሀገራችን ሰዎች ለአካል ጉዳት የሚጋለጡባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም በዋንኛነት ግን የማህበረሰቡ የኑሮ ዝቅተኛ ደረጃነት የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በተለይም ህጻናት በቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ለአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተጋላጭነት ከፍተኛ ነው። እናቶች በኑሮአቸው ደሀ ሆነው በቂና ተመጣጣኝ ምግብ የማያገኙ ከሆነ ደግሞ ልጆቻቸውን በበቂ ሁኔታ መመገብ ስለማይችሉ ልጆቻቸው ለአካላዊም ሆነ ለአእምሯዊ ዝግመት የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ ጦርነቶች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ድርቅና ረሀብ፣ ኋላ ቀር አመጋገብ፣ ንጹህ ውሃ ማጣት፣ የትራፊክ አደጋዎች፣ በወቅቱ በቂ ህክምና ያለማግኘትና የመረጃ እጦት የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ ከዓለም ጤና ድርጅት እ.ኤ.አ በ2018 የወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየአመቱ ከ210 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በስጋ ደዌ በሽታ የሚያዙ ሲሆን፣ በአፍሪካ ደግሞ 20 ሺ ያህሉ በየአመቱ በበሽታው ይጠቃሉ። የስጋ ደዌ በሽታ በአብዛኛው ቆዳንና የነርቭ ህዋሳትን ያጠቃል፤ የህመሙ መንስኤም ማይኮባክቴሪያ ሌፕሬ (Mycobacteria leprae) የተባለ ባክቴሪያ ዝርያ ነው።

> **ለህመሙ የሚያጋልጡትና መተላለፊያዎቹ ድህነት እና በስጋ ደዌ ታም ካልታከመ ሰው ጋር አየር በበቂ ሁኔታ በማይዘዋወርበት ቤት ተፋፍጎ መኖር ናቸው። ይህም ያልታከሙ ህሙማን ባሉበት ክፍል አየሩ እንዲታመቅና ባክቴሪያው በአንድ አካባቢ ለረዥም ጊዜ ተከማችቶ ለስጋ ደዌ ህመም ያጋልጣል**

ባክቴሪያው የበሽታው መንስኤ መሆኑም እኤአ በ1873 በኖርዌይ ተወላጁ ጌርሃርድ አርማወር ሃንሰን መታወቁን መረጃዎች ይጠቁማል። የበሽታው አምጪ ተህዋስ ቢታወቅም፣ በሳይንሳዊ ፍኖት ዘመናዊ መድኃኒት የተገኘለት ግን እ.ኤ.አ በ1941 በአሜሪካዊው ባይ ፈጌት ነው። በሽታ አምጪ ተህዋሱ ደካማና ለመራባት የሚወስደው ጊዜም ረዥም ሲሆን፤ በተህዋሱ በተጠቃ ሰው ውስጥ ምንም ምልክት ሳያሳይ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ሊቆይ ይችላል፡፡ በሁሉም የኑሮ ደረጃና የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶችንና ሴቶችን ሊያጠቃ ይችላል።

ለህመሙ የሚያጋልጡትና መተላለፊያዎቹ ድህነት እና በስጋ ደዌ ታሞ ካልታከመ ሰው ጋር አየር በበቂ ሁኔታ በማይዘዋወርበት ቤት ተፋፍጎ መኖር ናቸው። ይህም ያልታከሙ ህሙማን ባሉበት ክፍል አየሩ እንዲታመቅና ባክቴሪያው በአንድ አካባቢ ለረዥም ጊዜ ተከማችቶ ለስጋ ደዌ ህመም ያጋልጣል። የበሽታው መከላከያ የታመመውን ሰው ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ እና ህፃናት ክትባት እንዲከተቡ ማድረግ ነው። አንድ ሰው የስጋ ደዌ ታማሚ መሆኑ ከተረጋገጠ ሁለት ወይም ሦስት ፀረ ተህዋስ (ባክቴሪያ) እንደ በሽታው ዓይነት ለስድስት ወርና ለአንድ ዓመት ይሰጠዋል።

የስጋ ደዌ በሽታ በቶሎ ካልታከመ በአካል ላይ ጉዳት ስለሚያስክትል ታማሚዎች በሕብረተሰቡ መገለል ሲደርስባቸው ቆይቷል። ይሁንና በታማሚዎች ላይ የሚደርሰው መገለልና አድልዎ አሁንም ያልተቀረፈ ቢሆንም በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ ለውጦች ይታያሉ። የስጋ ደዌ ታካሚዎች አድልዎና መገለል የሚደርስባቸው በማህበረሰቡ ብቻ ባለመሆኑ በህክምና ቦታዎች ላይ የሚሰጣቸው አገልግሎት ልዩ ትኩረትን የሚሻ እንደመሆኑ መጠን ርህራሄ፣ አክብሮትና እንክብካቤ የተሞላበት ሊሆን ይገባል፡፡

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ ዜጎች እንዲቋቋሙና ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፤ በተለይም የአካል ጉዳተኞች እኩል እድልና ሙሉ ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ ማስቻል ከዋነኛ ተልዕኮዎቹ መካከል አንዱ ነው፡፡ “የሥጋ ደዌን በሽታ - አሁንም አንዘንጋው!” በሚል መሪ ቃል በአገራችን ለ24ኛ ጊዜና በዓለም ለ69ኛ ጊዜ ለሚከበረው የዓለም ሥጋ ደዌ ቀን ይህ ተልእኮ ሊሳካ የሚችለው የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች በዚሁ አግባብ ጥያቄዎቻቸው እና ፍላጎቶቻቸው ተገቢውን ምላሽ ማግኘት ሲችሉ ነው፡፡ ዘላቂነት ያለው በጊዜያዊ ድጋፍ ላይ ብቻ ያልተመሰረተ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ደግሞ ዋነኛው የተጠቃሚነት ማሳያ መንገድ ነው፡፡

የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ላይ የሚደርሰው መድልዎ እና መገለል በዋናነት ከግንዛቤ ማነስ የሚመጣ ችግር መሆኑን በመገንዘብ ቤተሰብ በታማሚ የደረሰው ችግር የጋራ ነው ብሎ ያለ ድካምና መሰልቸት መንከባከብ አለበት። በዋናነትም መገናኛ ብዙሃን ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በማከናወን ሕብረተሰቡ ስለ ስጋ ደዌ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥ በትኩረት መሥራት አለባቸው፡፡

በተጨማሪም በስጋ ደዌ የተጠቃን ሰው እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል በተናጠልም ሆነ በጋራ መርዳትና ለተጎጂዎችና ለቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ፍቅርና አክብሮት ማሳየት ሰብዓዊ ግዴታው መሆኑን በመገንዘብ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክትና ከኢትዮጵያ ስጋ ደዌ ተጠቂዎች ማህበር ጋር በባለቤትነትና በቅንጅት እንዲሰራ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥሪ ያቀርባል፡፡

## አማራ ክልል

በከሳሽ ወ/ሮ ሽብሬ አሰፋ እና በተከሳሽ በአቶ ዳዊት አበራ መካከል ስለአለው የፍትሐ-ብሔር ክርክር ጉዳይ አቶ ዳዊት አበራ ክስ የተመሰረተበት መሆኑን አውቆ እንዲቀርብ፤ የማይቀርብ ከሆነ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ መሆኑን አውቆ ለጥር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ በ3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርብ ሲል የአሳግርት ወረዳ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በሰብክመ ጠ/ፍ/ቤት በሰ/ሸ/ዞን አስ/የአሳ/ወ/ፍ/ቤት የፍ/ዳ/አ/አሰጣጥ ቡድን**

## ኦሮሚያ ክልል

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-73845 ኦሮ የሆነ ሊብሬ ጠፍቶብኛል ብለው ባለንብረቱ አቶ አደም ሐጅ በቀን 04/05/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በዚህ መሠረት ይህንን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ /የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የሻሸመኔ ከተማ ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

አመልካች አቶ ያብባል ማናዬ እና ተከሳሽ አቶ አለማየሁ ፈይሳ መካከል ያለውን የገንዘብ ክርክር አስመልክቶ ተከሰው እየተፈለጉ መሆንዎን አውቀው በቀጠሮ ቀን 18/05/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰአት ላይ እንድትቀርቡ የአሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የአሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ጉዳይ ቡድን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

ከሳሽ/አመልካች አቶ ክብሬ ብዙነህ ካሴ እና በተከሳሽ/ተጠሪ ወ/ሮ ቲና ፋንቱ ለማ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃ/ቃ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ22/05/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

## የሙያ ምዝገባና ፈቃድ መጥፋት ማስታወቂያ

ዶ/ር አብዱልአዚዝ አቡበከር ሸሪፍ የሙያ ደረጃ consultant Medical specialist (Inte.Medicine, hematology) በሙያ ምዝገባ ቁጥር CMSIMH=50/2009 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒት፣የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የተመዘገበ ሲሆን የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ጠፋብኝ ብለው አመልክተዋል። ስለሆነም የተጠቀሰውን የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ወድቆ ያገኘ ወይንም በእዳ ይዤዋለሁ የሚል በአንድ ወር ጊዜ ካላመለከተ ተለዋጭ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒት የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ ስመኝ ሞላ እና በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ቼኔዳ አኑዋፈ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ17/5/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ አቶ ሰለሞን ማሞ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ሶፊያ አህመድ መሐመድ መካከል ስላለው የቤተሰብ ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላፍቶ ምድብ 7ኛ ቤተሰብ ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው በ22/5/2015 ዓ.ም በ3፡40 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/አመልካች ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በተከሳሽ/ተጠሪ ረ/ኮሚሽነር ገዛኸኝ ገ/ህይወት ተማኑ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃ/ቃ ምድብ 6ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ17/05/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፦ www.press.et
ፌስቡክ፦ Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ከዋልያዎቹ ደካማ የቻን ቆይታ ጀርባ መታየት ያለባቸው ነጥቦች

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) በአልጄሪያ እየተካሄደ በሚገኘው የቻን ዋንጫ ለሶስተኛ ጊዜ መሳተፍ ቢችሉም የምድብ ጨዋታዎችን መሻገር ሳይችሉ በጊዜ ተሰናብተዋል። ይህ ቡድን ወደ አልጄሪያ ከመጓዙ በፊት ቢያንስ ከምድብ የማለፍ ተስፋ የተጣለበት ነበር። አሰልጣኝ ውበቱ አባተም ከወራት በፊት ተጨማሪ የሁለት ዓመት ኮንትራት ሲሰጣቸው በዚህ ውድድር ከቀደሙት ሁለት ተሳትፎዎች የተሻለ ስኬት የማስመዝገብ ኃላፊነት እንደተሰጣቸው አይዘነጋም። ያምሆኖ በውድድሩ እጅግ ደካማው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ነው የታየው።



ዋልያዎቹ የምድብ ጨዋታቸውን ደካማ ተደርጋ ከተቆጠረችው ሞዛምቢክ 0ለ0 ከመለያየት ውጪ በአልጄሪያ 1ለ0፣ በሊቢያ ደግሞ 3ለ1 ተሸንፈው ውድድሩን ቋጭተዋል። ይህም የኢትዮጵያን ሶስተኛ የቻን ተሳትፎ ካለፉት ሁለት ተሳትፎዎች የባሰ እንጂ የተሻለ ስኬት እንዳያስመዘግብ አድርጎታል። አሰልጣኝ ውበቱም የተሻለ ስኬት ያስመዘግባሉ ተብሎ ተስፋ ቢጣልባቸውም በመጀመሪያው ተሳትፎ አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው እንዲሁም በሁለተኛው ተሳትፎ አሰልጣኝ ዮሃንስ ሳህሌ ካስመዘገቡት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ሳይችሉ ቀርተዋል። ከውጤቱም በላይ ዋልያዎቹ በሜዳ ላይ እንቅስቃሴና በአጠቃላይ የነበሩባቸው በርካታ ክፍተቶች የኢትዮጵያን እግር ኳስ ደረጃ ቁልጭ አድርጎ ከማሳየት በዘለለ ከወቀሳ አላዳናቸውም። ለዋልያዎቹ ጥሩ የማይባል የቻን ውድድር ቆይታ ከእግር ኳሱ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ባሻገር መታየት የሚገባቸው ክፍተቶችም አገርን ዋጋ ማስከፈላቸው አልቀረም።

ዋልያዎቹ በተለይም በመጀመሪያው የሞዛምቢክ ጨዋታ አሸንፈው የበለጠ መነቃቃት መፍጠር የሚችሉበት እድል መምከኑ ብዙዎችን አስቆጭቷል። በአጠቃላይ ቡድኑ በቀጣይ ጨዋታዎች ላይ ለመፍረክረኩም የመጀመሪያው ጨዋታ የራሱ ተጽእኖ ነበረው። በዚህ ጨዋታ ዋልያዎቹ በርካታ የግብ እድል ቢፈጥሩም ኳስና መረብ ማገናኘት አልቻሉም። ለዚህም ቡድኑ ልምድና ብቃቱ ያለው ጨራሽ አጥቂ ማጣቱ ዋጋ አስከፍሎታል። ባለፉት በርካታ ዓመታት የዋልያዎቹ ግብ አዳኝ የሆነው ጌታነህ ከበደ ከአሰልጣኝ ውበቱ ጋር የገቡበት እሰጥ አገባ ለተከፈለው ዋጋ ዋነኞቹ ተጠያቂዎች ናቸው። ጌታነህና አሰልጣኝ ውበቱ ከዚህ ቀደም በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት በቻን ቡድኑ ምርጫ ላይ መፈጠር አልነበረበትም። ወሳኙ አጥቂ ጥሪ ከተደረገለት ቀን ዘግይቶ በመምጣቱ አሰልጣኙ በዲስፕሊን ምክንያት እንደቀነሱት መናገራቸው ይታወቃል። በመጀመሪያ ተጫዋቹ የአሰልጣኙን መመሪያ ማክበር ነበረበት። ቀጥሎም አሰልጣኙ ተጫዋቹን ከቡድኑ ከመቀነስ በፊት ለአገር ውጤት ሲባል ነገሮችን ግራና ቀኝ መመልከት ነበረባቸው። አንዳንዴ ነገሮች ደረቅ በሆኑ መርሆዎች ብቻ ሲመሩ እንዲህ አይነት ጣጣ እንደሚያመጡ ቆም ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው። ፌዴሬሽኑም ለእንዲህ አይነት ችግሮች በአሰልጣኙ ስራ ጣልቃ መግባት ተገቢ ባይሆንም ሁለቱንም አካላት ለማግባባት ያደረገውን ጥረት በይፋ አላየንም። ዞሮ ዞሮ በሁለቱ አካላት እሰጥ አገባ የተጎዱት ግለሰቦች ሳይሆኑ አገር ናት።

ቴክኒካዊ የሆኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ለመመልከት አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ ወሳኝ ነጥቦችን ማንሳት የግድ ነው። በቡድኑ ውስጥ ለእያንዳንዱ ቦታ ምርጡን ተጫዋች የመምረጥ እና ጠንካራ አንድ ቡድን የማቀናጀት ጽንሰ ሃሳብ የእግርኳስ ዓለምን የለወጠ እና የገዛ የዘመኑ ምርጥ ዕቅድ ነው። አንድ ቡድን እቅድ ከሌለው ሁሌም መፍረክረኩ አይቀርም። መሸነፍ ተፈጥሯዊ ቢሆንም ትልቁ ችግር የሽንፈቱን ምክንያት አለማወቅ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የሁልጊዜም ችግር ደግሞ ሲያሸንፍም ያሸነፈበትን ምክንያት ሲሸነፍም የተሸነፈበትን ምክንያት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አለማወቁ ነው። የሽንፈትን ምክንያት ማወቅ ወደ ዋናው እቅድ ይወስድሀል። ማስተካከል የሚገባን ነገር ለማስተካከልና የነገን የቤት ስራ ለመስራት ትልቅ ግብአት ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ትልቁ ችግር ለሚፈለገው የጨዋታ እቅድ ተጫዋቾችን አለማዘጋጀት እና ተጫዋቾችን ወደ ሚፈለገው ዓላማ አለማምጣት ነው። በእግርኳስ ጨዋታ ውስጥ ትልቁ ነገር የቡድን የመጫወቻ ቅርፅ መፍጠር እና ይህንን ቅርፅ ጠብቆ መጓዝ መቻል ነው። የሜዳ ውስጥ የጨዋታ ቅርፅን ጠብቆ መጓዝ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ትልቁ ችግር ነው።

አንድ ቡድን የሚጫወትበትን የጨዋታ ቅርፅ ጠብቆ መጓዝ እና በሌሎች የግል (ተናጠል)፥ እንቅስቃሴዎች አለመዋጥ ዋነኛ ዓላማው መሆን አለበት። ቡድን ማለት ያለውን ነገር የሚጠብቅ ማለት ነው። ይህ እሳቤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ የጎደለ አንድ ትልቅ ክፍተት ነው።

አንድ ተጫዋች በቦታው የሚጫወትበት ዓላማ ሲኖረው ነገሮች ቀላል ናቸው። የኳሱን ሂደት ወደ ፊት እንዲያራምዱ ለማስቻል ሶስት መአዘኖች ወይም ኳስ የመቀበያ አማራጭ በመፍጠር ለኳስ ተቀባዩ እና አቀባዩ ቦታ እና ጊዜ በመግዛት በማንኛውም ጊዜ በርካታ የቅብብል አማራጮችን በመፍጠር መቀጠል ማለት ነው። ከዚያም ተጋጣሚውን ወደ ኳሱ በመሳብ ተጫዋቹ የሚቀጥለውን ቅብብል ለመቀጠል የቡድን ጓደኛውን በሌላ ቦታ ነፃ ያወጣዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የተጫዋች ብቃት ችግር ሳይሆን ተጫዋቹን የማብቃት መሰረታዊ የእሳቤ ክፍተት አለ። ይህንን ማሳደግ፣ መስራት እና መሸከም የሚችል ሃሳብ ግን አሰልጣኞች ቢቀያየሩም መቀየር እንዳልቻለ ከዋልያዎቹ የቻን ቆይታ የበለጠ በግልጽ የሚያሳይ ምሳሌ ሊኖር አይችልም።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር

### በየሰምንቱ የሚታተም

# ሸማች መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አማራጭና ወጥ አሰራር ይሻሉ

**በአስምነህ ቸርነት**

ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት አባሎቻቸውንና ማህበረሰቡን ከኑሮ ውድነት ፈተና ለመታደግ በሚያደርጉት ጥረት በቂ የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርቶች አቅርቦት ያስፈልጋቸዋል። ለዚህ ደግሞ የዩኒየናቸው ጥንካሬ ወሳኝ ነው። ዩኒየን ያስፈለገበትም ዋናው ምክንያት አንድም ገበያ አፈላልጎ በቂ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ለመሰረታዊ አባላት ለማቅረብና ከዚህ ባለፈ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦትን በማሳደግና የአባላት አቅምን በመገንባት ረገድ እንዲደግፋቸው ነው። ሆኖም ግን አንድ ዩኒየን በተለያዩ ምክንያቶች በአግባቡ ገበያ አፈላልጎ ምርቶች በሚፈለገው ደረጃ ለመሰረታዊ አባላቱ ማቅረብ ካልቻለ በአባል ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበረት ላይ ተጽእኖ መፍጠሩ የማይቀር ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የሚገኘው የኮሪያ ሰፈር ሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

የኮሪያ ዘማቾች በብዛት በሚኖሩበትና ብዙው ማህበረሰብ በነፍስ ወከፍ ገቢ በሚተዳደርበት በዚህ መንደር ማህበረሰቡን ከኑሮ ውድነት ለመታደግ በ2000 ዓ.ም የተመሰረተው የኮሪያ ሰፈር ሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ ኅብረት ሥራ ማህበር እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በአሁኑ ግዜም ወንድ 854 ሴት ሁለት ሺ 113 በድምሩ ሁለት ሺ 960 አባላት ማቀፍና ለ113 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል።

ማህበረሰቡ ለገና በዓል ስጋ በአነስተኛ ሽያጭ እንዲያገኝ ማህበሩ በሥጋ ቤት የኪራይ ዋጋ ላይ የወሩን ቅናሽ በማድረግ ስጋ አቅራቢው በቅናሽ ኪሎ ስጋ በ350 ብር እንዲሸጥ በማድረግ በዕለቱ እስከ 15 ሰንጋ ድረስ በማቅረብ ማህበረሰብ የሚያረካ ስራ ሰርቷል። ከዚህ ሌላ ማህበሩ ለገናም ሆነ ለጥምቀት በዓላት ለማህበረሰቡ 15 ኩንታል ሽንኩርት፣ አራት ሺ 200 እንቁላል፣ 100 ኪሎ ቅቤ፣ ዱቄት ከድጎማ ውጪ 160 ኩንታል፣ 100 ኩንታል ነጭ ጤፍ፣ ወደ 600 ካርቶን ፈሳሽ ዘይት፣ 8000 ባለ 20 ሊትር የድጎማ ዘይትና ስኳር በነፍስ ወከፍ ሁለት ኪሎ ተደራሽ አድርጓል።

ለማህበሩ ትልቅ እርካታ ከሚሰጠው ተግባራቱ መካከል ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ህጻናት ቢሮ ጋር በመተሳሰር ለእናቶችና ህጻናት የሚሰጠው የምገባ አገልግሎት ተጠቃሽ ነው። ምንም የሚላስ የሚቀመስ ለሌላቸው እናቶች፣ ነፍሰጡሮች፣ ህጻናት መንግስት ለሚሰጠው የድጎማ ምገባ መርሀ ግብር ከጅማሮው አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ያለምንም መቆራረጥ ምርቶች በማቅረብ እየተሳተፈ ይገኛል።

የድጎማ ምርቶች በንግድና ኢንዱስትሪ በኩል ግዜውን ጠብቆ የሚመጣ እንደመሆኑ ማህበሩ በተሰጠው ኮታ መሰረት ግዢ የመፈጸምና ተረክቦ የማሰራጨት ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው። ነገር ግን ከግዜ ወደ ግዜ እየቀነሰ ያለው ኮታና የስርጭት ጣልቃገብነት መኖር በማህበረሰቡ በኩል ጥያቄ እያስነሳ በመሆኑ አሳሳቢ ሆኖበታል።

የድጎማ ምርት ብዙ ግዜ በሸማች ማህበራትና በማህበረሰቡ መካከል አለመተማመን እንዲኖር እያደረገ ነው በማለት የሚያስረዱት የቦርዱ ሰብሳቢ አቶ ዳኜ ከበደ፤ አንዳንድ የንግድና ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች በተለያዩ ሰበቦች ደብዳቤ በመጻፍ ምርት የሚወስዱበት አሰራር የሸማች ማህበራትን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ በመሆኑ በንግድና ኢንዱስትሪ በኩል ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ቢኖር መልካም ነው በማለት ሃሳባቸውን ያጋራሉ።

በጥቅሉ ሲታይ ግን የኮሪያ ሰፈር ሸማች ኅብረት ስራ ማህበር እየሰጠ ያለው አገልግሎት አጥጋቢ ነው ብሎ ማለት አይቻልም የሚሉት የማህበሩ ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ዳኜ፤ ለዚህ ምክንያታቸውን ሲያስረዱ የካ ዩኒየን በአመራር ክፍተት በሙሉ አቅም ወደ ስራ የመግባት ችግር ስላለው ለመሰረታዊ ሸማች አባላት የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርት በአጥጋቢ ደረጃ እየቀረበ አለመሆኑን ይገልጻሉ።

‹‹መሰረታዊ አባል ከዩኒየን ካልሆነ ግዢ መፈጸም አይችልም የሚለው መመሪያ ዩኒየን ካላቀረበ ከሌላ ግዢ እንዲፈጸም አማራጭ አሰራር አለመኖሩ ክፍተት ነው።›› የሚሉት ኃላፊው፤ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለማስገባት የሚያስችል በቂ ካፒታል ቢኖረንም የአሰራር ሁኔታዎች አመቺ ባለመሆናቸው ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ በሚገባን ልክ ማድረስ አልቻልንም ይላሉ።

ዩኒየኑ ምርት ማቅረብ ካልቻለ መሰረታዊ ማህበራት ከኪራይ ሰብሳቢነት በጸዳ ሁኔታ ከየትኛው የምርት አቅራቢ ጋር ህጋዊ ግብይት መፈጸም እንደሚችሉ ግልጽ መፍትሄ አብሮ መቀመጥ አለበት ሲሉ ያስረዳሉ። ከሌላ አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ግብይት መፈጸም ይችላሉ ከተባለም እነዛ ኅብረት ስራ ማህበራት እነማን እንደሆኑ በግልጽ በማስቀመጥ ወጥ አሰራር ሊዘረጋ ይገባል ባይ ናቸው።

ከዩኒየን ጋር ብቻ ግብይት እንዲፈጸም ከሚለው ሳጥን በመውጣት በራሳቸው ግብይት ለመፈጸም የሚፍጨረጨሩ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየካም ሆነ በሌሎች ክፍለ ከተማዎች በብዛት እንደመኖራቸው እናንተስ ለተባሉት ጥያቄ አቶ ዳኜ መልሳቸው “መሰረታዊ ሸማቾች በራሳቸው ግብይት የሚፈጽሙት ደፍረው የመጣ ይምጣ ብለው ነው። እኛ ግን ከዩኒየን ውጭ ግብይት ለመፈጸም በፍርሃት ቆፈን ተይዘናል። ለህብረተሰባችን ተገቢ የሆነ አገልግሎት መስጠት እንድንችል ከተፈለገ አሁን ያለው ጉራማይሌ አሰራር ሊስተካከል ይገባል” ሲሉ ያስረዳሉ።

ማህበሩ ውስንነት ያለው ቢሆንም በእሁድ ገበያ አትክልትና ፍራፍሬ በማቅረብ ተሳትፎ ያደርጋል። ተሳትፎው ግን ለይምሰል ያህል ነው ይላሉ። “እኛም ሆንን ሌሎች ብዙ ሸማች መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት በማህበረሰቡ የሚፈለጉትን ምርቶች በአግባቡ ይዘን ለማቅረብ የተቸገርንበት ሁኔታ በመኖሩ ተደራሽነታችን ውስንነት አለው። ከፈለገው አማርጦ ዋጋ ከሚቀንሱትና ደረሰኝ ከሌላቸው አቅራቢዎች አትክልትና ፍራፍሬ ከሚያመጣው ከነጋዴው ጋር አብሮ ቀርቦ በዋጋና ጥራት ተወዳዳሪ ለመሆን ስለተቸገርን መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል ባይ ናቸው።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et